የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ሙሉ የሆነውን የእምነት ሕይወት መማር
- የአብሮነት ስልት
- ምሳሌያዊ ግንኙነትን ማሳደግ
- ትክክለኛውን ምሳሌያዊ ግንኙነት መለየት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ።

- መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች የእምነት መሠረት እንዲሆኑ ማስተማር የሚያስፈልግበትን ምክንያቶች መዘርዘር ትችላለህ።
- በአብሮነትና በክርስቲያናዊ ምግባ መካከል ያለውን ዝምድና መግለጽ ትችላለህ።
- በክርስቲያናዊ ምግባ ውስጥ ምሳሌያዊ ግንኙነቶች ምን እንደሆኑ መተንተን ትችላለህ።
- በክርስቲያናዊ ምግባ ውስጥ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ሰዎች እንዴት ያሉ ሰዎች እንደሆኑ መናገር ትችላለህ።

---

የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

# ሙሉ የሆነውን የእምነት ሕይወት መማር

*ዓላማ 1 ሙሉ የሆነውን የእምነት ሕይወት እንዴት እንደምንማር የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

እንዴት ክርስቲያን እንደሆንህ ትዝ ይልሃል? በዚያን ወቅት የተሰበከልህን ወንጌል አላመንህም? የቀረበልህን ደኅንነት አልተቀበልህም? ሕይወትህን ለክርስቶስ አልሰጠህም? በእርግጥ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አድርገሃል። ሁላችንም ለተሰበከልን ወንጌል ምላሽ የሰጠነው በእምነት አማካይነት ነው። በዚህ ምክንያት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መግቢያ በር የሆነውን አዲስ ልደት ተቀብለናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን በሄድን ቁጥር፥ ክርስቶስን እየመሰልን እንደመጣን አስተውለናል። ስለዚህ ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበቀ በሄደ ቁጥር፥ የእርሱን ባሕርይና አመለካከት በሕይወታችን እያንጸባረቅን እንሄዳለን። ወንጌልን በእምነት በተቀበልን ጊዜ በእምነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት መኖር ጀምረናል፤ ይህም ሕይወት ኢየሱስን ለመምሰል ሙሉ ሆኖ የሚያድግ የእምነት ሕይወት ነው። ሕያው በሆነ እምነት ላይ የተመሠረተው ይህ ሙሉ ሕይወት የእምነት ሕይወት ይባላል። ሙሉ የሆነውን ሕይወት በእምነት አማካይነት የምናገኘው እንዴት





ነው? ይህ የእምነት ሕይወት የተገኘውስ ከምንድን ነው? ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት መኖር የምንማረው እንዴት ነው?

ሙሉ የሆነውን ሕይወት የሚያስገኘው እምነት የሚገኘው ከዕውቀትና ከሕይወት ማለትም እምነት በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ሲገለጥና ሲታይ እንደሆነ ይታወቃል። እግዚአብሔር እውነት የሆነውን የእርሱን ፈቃድ ገልጦልናል፤ ይህንን እውነት ልንቀበለው ወይም ሳንቀበለው እንችላለን። ይህ የእግዚአብሔርን ጠባይና ባሕርይ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ዓላማ የሚገልጸው እውነት በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ተጽፎ፥ ተጠብቆና ተላልፎ ተሰጥቶናል። እምነትን እንዲያድግና እንዲበስል የሚያደርገው ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው እውነት ነው፤ ይህ እውነት ደግሞ የዕውቀት ምንጭ ነው።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ትእዛዛዊ (ወይም ሕግጋታዊ) ባሕርይ አላቸው። ለምሳሌ በዐሥርቱ ትእዛዛት ላይ እግዚአብሔር እንዴት ያለ አምላክ እንደሆነ፥ ከሕዝቡ ምን እንደሚጠብቅና እግዚአብሔርን መታዘዝ ምን በረከት እንደሚያመጣ እንመለከታለን። አንዳንድ እውነቶች ደግሞ አሳቤያዊ ባሕርይ አላቸው፤ እነዚህ አሳቤዎች አጠቃላይ ሲሆኑ የተወለዱትም የእርስ በርስ ዝምድና ካላቸው ልማዶች ነው። እግዚአብሔር ሙሴ ከጻፋቸው መጻሕፍት ውስጥ በአንዱ ላይ ቅዱስ የሆነውን ነገር ቅዱስ ካልሆነው ነገር እንዴት ለይቶ እንዳስቀመጠ በጥንቃቄ ስንመለከት የቅድስናን አሳቤ እንማራለን። አንዳንድ እውነቶች በሕይወታችን ልንለማመዳቸው የሚገቡ እውነቶች በመሆናቸው መርሃዊ ጠባይ አላቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔርን በሙሉ ሁለንተናችን እንድንወድ የተሰጠን ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት የሚገዛ ሲሆን ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት መሠረት የሚሆነውም ይሄው መርህ ነው። እንግዲህ ትእዛዛት፥ አሳቤዎችና መርሆች በእምነት ላይ ለተመሠረተ ዕውቀት መሠረት ናቸው። በክርስቶስ ሙሉ ሰው ሆኖ ለማደግ እነዚህን ነገሮች በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህ ዕውቀት ከሌለን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው የእምነት ሕይወት እንዴት ያለ እንደሆነ ማወቅ አንችልም።

በጽሑፍ አስፍሮ ከሰጠን እውነት በተጨማሪ፥ እግዚአብሔር ሕያው በሆነ መንገድ ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ገልጦአል። ዮሐንስ ሲናገር እንዲህ ይላል፦ «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፤ . . . ክብሩን አየን» (ዮሐ. 1፥14)። ጴጥሮስ ደግሞ የክርስቶስን ግርማ፥ ክብርና ኀይል በዐይኑ ያየ ምስክር መሆኑን ይናገራል (2ጴጥ. 1፥16–18)፤ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ የእርሱን ምሳሌነት እንድንከተል ሕይወቱን ምሳሌ አድርጎ እንዳቀረበልን ጴጥሮስ ይመሰክራል (1ጴጥ. 2፥20–25)። ኢየሱስ ሙሉና የተትረፈረፈ ሕይወትን እንዴት እንደምንኖር እንዲሁም እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሕይወት እንዴት እንደምንኖር አሳይቶናል። የኢየሱስ ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የእምነት ሕይወት ምሳሌ ነው (ኢየሱስ የአብን ፈቃድ ለመታዘዝና ለአብ ፈቃድ ለመገዛት ፈቃደኛ ነበር፤ እግዚአብሔር ሲያድናቸው የፈቀደውን ሰዎች ለመወደድ ፈቃደኛ ነበር)።

ሥርዐት አይመችህም። በአንተ ባሕል ውስጥ ትክክለኛውን ያመጋገብ ሥርዐት የተማርኸው ሌሎችን በማየትና ያየኸውን በማድረግ ነው። ከአንተ በተለየ ሁኔታ የሚመገቡ ሰዎችን አይተህ ተገርመህ ይሆናል።

እያንዳንዱ ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ የአመጋገብ ሥርዐት አለው። በአንዱ ኅብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የአመጋገብ ሥርዐት በሌላው ኅብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት የለውም፤ እንዲያውም በአንዱ ኅብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የአመጋገብ ሥርዐት ለሌላው ኅብረተሰብ የሚያስቀጣና የሚያስደነግጥ ነው። በተለያየ ባሕል ውስጥ ያደጉ ሰዎች የተለያየ ባሕርይ ሲያሳዩ አስተውለህ ይሆናል። ሁሉም የየራሳቸው የሆነ መለያ ባሕርይ አላቸው። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ሕፃናት ያደጉበትን ኅብረተሰብ የአኗኗር ሥርዐት ተምረው ሲያድጉ፥ በሌላ ኅብረተሰብ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ሕፃናት ደግሞ ከእነዚህ በተለየ ሁኔታ ሲኖሩ ይታያል። እንዲህ ያለው ልዩነት ሊፈጠር የቻለው እያንዳንዱ ሰው ያደገበትን ኅብረተሰብ ባሕልና አኗኗር በአብሮነት (በመኖር) ስለሚማር ነው።

እናት መፍቻ ቋንቋህን የምትማረው እንዴት ነው? ምናልባት ሁልጊዜ ስትናገረው እንደኖርህ ልትናገር ትችላለህ። ምናልባትም ተምረህ ካወቅሃቸው ቋንቋዎች ይልቅ እናት መፍቻ ቋንቋህን ስትናገር የበለጠ አቀላጥፈህ እንደምትናገር ልትናገር ትችላለህ። ሁልጊዜ ስትናገረው ስለኖርህ ያለ ትምህርት ያወቅኸው ሊመስልህ ይችላል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ እናት መፍቻ ቋንቋህን ያወቅኸው ተምረህ ነው። ልክ እንደተወለድህ ሌላ ቋንቋ ወደሚነገርበት ስፍራ እንድትኖር ብትወሰድ ኖሮ ሁኔታው ምን ይመስል ነበር? እንዲህ ዐይነት ዕድል አጋጥሞህ ቢሆን ኖሮ፥ አሁን የምትናገረውን ቋንቋ ሳይሆን ተወስደህ ያደግህበትን ስፍራ ቋንቋ ትናገር ነበር፤ ቋንቋን የምንማረው በአብሮነት ነው።

(3). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ሁለት ወይም ሦስት የአብሮነት ምሳሌ ሂደቶችን ዘርዝር።

## የአብሮነት ፍቺ

*ዓላማ 4 አብሮነትን የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ለይ።*

አብሮነት የሚከሰተው ሰዎች ተጨባጭ በሆነ የሕይወት ዓለም ውስጥ አብረው ሲኖሩ ነው። ባሕርያችን የሚቀረጸው ተወልደን ባደግንበት ኅብረተሰብ መሠረት ነው። ሌሎች ሰዎች የሚኖሩትን ሕይወት እያየን የአካባቢያችንን ሥርዐተ እሴት እንማራለን። ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነትና አንድነት የራሱ ጠባይ ስላለው፥ ከአብሮነት የምንማረው ትምህርት አብዛኛውን ጊዜ ያልተደራጀ፥ መልክና ሥርዐት ያልያዘ ነው። አሁን የያዝነውን የአኗኗር ሥርዓተ እሴት የወረስነው እንዳለ ነው፤ ወይም አብሮ በመኖር ያገኘነው ነው።





አብሮነትን ከሌሎች የምንማረው በማየት ነው፤ ሌሎች የሚኖሩትን ሕይወት በተግባር በማየት ነው። ሰዎች አንድን ነገር የሚማሩት የሌሎችን ሰዎች ኑሮ በማየት ነው፤ ቀደም ባለው ትምህርታችን አንድ ነጋዴ የንግድን ሥርዐት የሚማረው መምህሩ የሚሠራውን በማየት እንደሆነ ተምረናል። አንድን ሕይወት የሚቀርጹ የሕይወት ዘይቤዎችና የአኗኗር ሥርዐቶች አብሮ በመኖር ብቻ ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋሉ፤ የአንድ ኅብረተሰብ አባላት የሕይወት ዘይቤን የሚማሩት በማየት ወይም አብሮ በመኖር ነው። አንድ ሰው (ተማሪ) በአካባቢው የሚሆነውን ነገር ወይም የሚያስተው ለውን ሕይወት በመመልከት እርሱም እንዳየው ዐይነት ለመኖር ይፈልጋል።

ከሌሎች ሰዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት መመሥረት የአብሮነት ትልቁ ባሕርይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው ከሌላ ሰው መማር የሚችለው የዚያን ሰው ሕይወት እርሱም ለመኖር የፈለገ እንደሆነ ነው። በሌላ አነጋገር አንዱ ለሌላው ምሳሌ ይሆናል። ምሳሌ በሚሆነውና በተማሪው መካከል የሚፈጠረው የቅርብ ግንኙነት «ተደጋግፎት» (ወይም ተደጋጋፊነት) ይባላል፤ ይህ ተደጋግፎት እርስ በርስ በመተሳሰብ፥ በመተማመን፥ በመተዋወቅና አንዱ ለሌላው እንደሚያስፈልግ በመረዳት ይገለጻል።

ልክ እንዲሁ በአብሮነት ውስጥ ተማሪው ምሳሌ የሚሆነውን ነገር ማግኘት አለበት። ሕይወት እንዲህ ያለውን ምሳሌነት አብዝቶ ሰጥቶናል። ፍሬያማና ውጤታማ ምሳሌዎች የሚታዩት በገሃዱ ዓለም ውስጥ በመሆኑ፥ ምሳሌዎችን የሚከተሉ ተማሪዎች እነርሱም በገሃዱ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ መሆን አለባቸው። ተማሪው ያየውን ምሳሌ ይከተላል። ተማሪው ያየውን ምሳሌ ለመከተል ሲሞክር የተማረውን ነገር እየተለማመደ ነው። ተማሪው ባየው ምሳሌ መሠረት እርሱም ሲኖር፥ ልክ ነኝ ወይስ ልክ አይደለሁም የሚለውን ለማረጋገጥ ወደ ምሳሌው ይመለከታል።

(4). ከላይ ከተጠቀሱት አራት አንቀጾች አብሮነትን ለመማር የሚያስፈልጉትን ነገሮች በትክክል የሚገልጹትን አራት ዐረፍተ ነገሮች ግለጽ።

## አብሮነት በተግባር

*ዓላማ 5 በአብሮነትና በክርስቲያናዊ ምግባ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

በአንድ በኩል ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት የምንማረው በአብሮነት ነው። ኢየሱስ የሰጠውን የተትረፈረፈ ሕይወት መኖር የምንማረው፥ ተወልደን ያደግንበትን ኅብረተሰብ ባሕልና ቋንቋ በምንማረው መሠረት ነው። ክርስቶስን ለመምሰል የሚያስፈልጉትን ባሕርያት የምንቀስመው፥ ሕይወታቸው የክርስቶስን ሕይወት ከሚመስል ሰዎች ጋር በምናደርገው የቅርብ ግንኙነት ነው።

ይህም ለሌሎች (ለልጆች) ትልቅ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በሙሉ ልባቸው እንዲጠብቁ ማለትም ለመንፈሳዊ ነገር ቦታ እንዲሰጡ ታዘዋል። በቤተሰባዊ ግንኙነታቸው ውስጥ ለመንፈሳዊ ነገር ትልቅ ቦታ በመስጠት እነዚህን ነገሮች ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ ታዘዋል። ቤታቸውን የሃይማኖት የእምነት ማእከል ማድረግ አለባቸው። ልክ እንዲሁ ክርስቲያኖችም ለክርስቶስ ሕይወት ምሳሌ መሆን አለባቸው።

ትንንሽ ቡድኖችና ኅብረቶች የግንኙነት መመሥረቻ ማእከሎች ናቸው። እነዚህ ቡድኖች ወይም ኅብረቶች የቤተሰብ አባላትን፥ ጎረቤቶችን፥ የቤተሰብ ጓደኞችን ሊያካትቱ ይችላሉ። በእነዚህ ቡድኖችና ኅብረቶች ውስጥ የሚሳተፉት አባላት መልካም ምሳሌነትን ሊያሳዩ ይችላሉ። ከሌላ ሰው ጋር የመሠረትከው እንዲህ ያለ ግንኙነት ትዝ ይልሀ ይሆናል። ያ ሰው በመንፈሳዊ ነገሩ ከአንተ በጣም የበሰለ ከሆነ ምሳሌ ሊሆንህ ይችላል፤ ወይም ደግሞ ያ ሰው እንዳንተ ያልበሰለ ከሆነ ምሳሌ ልትሆነው ትችላለህ።

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተማሪ እንዲሆኑ የአስተማሪነት ስጦታ ያላቸውን ሰዎች እንዳስቀመጠ በዚህ ትምህርት ውስጥ አስተውለህ ይሆናል። ስለ መንፈሳዊ ስጦታ የሚናገሩት ክፍሎች ሁሉ እግዚአብሔር የአስተማሪነት ስጦታን ለቤተክርስቲያን እንደሰጠ ያወሳሉ። በቤተክርስቲያን ውስጥ በአስተማሪነት የሚያገለግሉ ሰዎች ምሳሌያዊ ሕይወትን የመኖር ኀላፊነት አለባቸው። አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በባሕርያቸው፥ በአመለካከታቸውና በኑሮ ዘይቤአቸው እማኳኑነት ሕያው በሆነ መንገድ የማስተማር ግዴታ እንዳለባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ (1ጢሞ. 4፥12)።

እንደ እውነቱ ከሆነ ከቤተክርስቲያን ባሕርይ የተነሣ፥ እያንዳንዱ አማኝ ለሌላው ምሳሌ መሆን አለበት። ጳውሎስ በቆሮንቶስ የሚገኙ አማኞችን ሲያሳስባቸው፥ እናንተ በዙሪያችሁ ላሉ ሰዎች የምትነበቡ መልእክት (ወይም ደብዳቤ) ናችሁ ይላቸዋል (2ቆሮ. 3፥1–3)። እንደ ጳውሎስ አባባል የቆሮንቶስ ሰዎች ለሌሎች የሚነበቡት በልባቸው እንደተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህም ማለት ለሚያያቸው ሰው ሁሉ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት ለሌሎች መታየት አለበት። በክርስቶስ አካል ውስጥ ጥብቅ ትስስር በመኖሩ ምሳሌያዊ ግንኙነት አለ። አንዳንድ ጊዜ እኛ ሳናውቀውና ልብ ሳንለው ሌሎች ሰዎች የእኛን ሕይወት ምሳሌ ሲያደርጉ ይገኛሉ። ሆኖም ከዚህ ይልቅ እኛ እያወቅነውና ልብ እያልነው ሌሎች ምሳሌ ሊያደርጉት የሚመኙትን ሕይወት ከሌሎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመመሥረት ማሳየት አለብን።

(12). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ቤተሰባዊ ግንኙነት በምሳሌያዊ ግንኙነት ውስጥ መኖር የሚገባውን ለማሳየት ዓይነተኛ ነው።
ለ. ክርስቲያኖች ዓይናቸውን በጌታ ላይ ማድረግ ስላለባቸው የሚያሳዩት ምሳሌያዊ ሕይወት ለሌሎች ጠቀሜታ የለውም።





ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆች ለልጆቻቸው በመንፈሳዊ እውነት ምሳሌ እንዲሆኑ ያዛል።
መ. ጠንካራ ወዳጅነት ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው።
ሠ. በቤተ ክርስቲያን ያሉ አስተማሪዎች ከሚሆኑት ይልቅ ለሚናገሩት ትልቅ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።
ረ. በቤተ ክርስቲያን ያሉ አስተማሪዎች ሰዎች ሊከተሉት የሚገባ ሕይወት እንዲኖሩ የተለየ ኃላፊነት አለባቸው።
ሰ. ክርስቲያኖች ሁሉ ሰዎች እንዲያዩት ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት መኖር አለባቸው።

ኢየሱስ «ተማሪ. . . እንደ አስተማሪው ይሆናል» በማለት የተናገረው ቃል ትልቅ እድናቆት የሚቸረው ቃል ነው። የክርስቲያናዊ ምገባ ዓላማ ሰዎች ክርስቶስን እንዲመስሉ መርዳት ሲሆን ይህን ተልዕኮውን ከግብ የሚያደርሰው የአብሮነት ስልት በመጠቀም ነው። ይህ ስልት ምሳሌያዊ ግንኙነትን በመመሥረት አስተማሪውን የሚመስሉ ተማሪዎችን የሚያፈራ ስልት ነው። የክርስቶስ አካል በሆኑ አማኞች መካከል ያለው የጋራ ግንኙነት መንፈሳዊ ዕድገትን ለማምጣት ትክክለኛው መንገድ ነው።

---

## የሙከራ ፈተና

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ከሆነው ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከአንዱ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን እንደ እምነት መሠረት አድርገን ማስተማራችን ቀዳማዊ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ያልተጠቀሰው ምክንያት የትኛው ነው?

ሀ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀቆች ለእምነት እውቀት መሠረት ናቸው።
ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀቆች እምነት እንዲያድግ የሚያደርጉ የእውቀት ምንጮች ናቸው።
ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀቆች የተፈጸሙ ሀቆች፣ እንደ እሳቤና አንዳን ዶች ደግሞ እንደ መርሆዎች ቀርበዋል።
መ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀቆች ሁሉ አካላዊነት ከሌላቸው የተሰጡ መገለ ጦች ናቸው።

2. እንደ ትምህርቱ አባባል ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የእምነት መሠረት አድርጎ ያስተምራል፤ ምክንያቱም. . .

ሀ. ሰዎች የሰነ ምግባር ሕይወት እንዲኖሩበት የምናደርግበት መንገድ ባለመኖሩ ነው።
ለ. ልንቀበላቸው ወይም ልንጥላቸው የምንችላቸው እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን እውነቶች በመሆናቸው ነው።

# 7 ሰዎች እንዲማሩ መርዳት

## ትምህርት

አማኑኤል ወደ ትምህርት ቤት በመሄዱና ትምህርቱም ጣፋጭ በመሆኑ ተደስቶአል። በመጀመሪያ የተሰጠው ሥራ ቀላል ነበር፤ ፊደል ማጥናት፥ ቁጥሮችን መለየት፥ ከ1 እስከ 10 መቁጠርና የራሱን ስም መጻፍ ነበር። ውሎ ሲያድር ግን የሚሰጠው ሥራ እየጠነከረ መጣ፤ የተጻፉ ነገሮችን በትክክል ማንበብ፥ መጻፍና የሂሳብ ጥያቄዎች መመለስ ነበር።

ፀሐይ በመማር ማስተማር ላይ የተሰጠውን ዐውደ ጥናት ከተካፈለች በኋላ ልጇ አማኑኤል ጥሩ ተማሪ እንደሆነ ተረዳች፥ የአማኑኤል አስተማሪ መምህርት ሔንሳ ልጆች እንዴት መማር እንደሚችሉ መርዳት ታውቃለች። እንዲሁም ትምህርት ጣፋጭ፥ አስተሳሰብን ፈታኝና ውጤታማ እንዴት እንደሚሆን ታውቃለች።

አስተማሪ ትምህርትን እንዴት እንደምንማር ትክክለኛውን አቅጣጫ ሲያሳየን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች መማር እንችላለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ አስተማሪዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት እንድንመረምር፥ ትርጉማቸውን እንድንለይና ከዕለት ተዕለት ኑሮአችን ጋር እንድናዛምድ አቅጣጫ ይጠቁሙናል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ሰዎችን እንዴት እንደምታስተምር፥ መጽሐፍ ቅዱሰን ስታጠና ቀድሞ የማታውቃቸውን ነገሮች እንዴት እንደምታውቅ፥ መጽሐፍ ቅዱሰን እንዴት እንደምታጠናና ትርጉም ያለው ትምህርትን እንዴት እንደምታዘጋጅ ትማራለህ።

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የማስተማር ተግባር
- ግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
- ስርዐታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
- ተማሪው ሊማር የሚገባውን ነገር በሚገባ ማቀድ





### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህንን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ።

- የማስተማር ተግባር ምን እንደሆነ ማብራራት ትችላለህ።
- በግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ያሉትን ሁለት የጥናት መመሪያዎች መግለጽ ትችላለህ።
- ተማሪው ሊማር የሚገባውን ነገር እንዴት ትርጉም ባለው መንገድ ሊማር እንደሚችል መግለጽ ትችላለህ።

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

## የማስተማር ተግባር

ባለፈው ትምህርታችን፥ በእምነት ላይ ስለ ተመሠረተ ሙሉ ሕይወት ተነጋግረን ነበር። በትምህርቱ ላይ እንዳየነው፥ አንድ ሰው ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደረጃ የሚደርሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ሲያገኝ እንደሆነና ይህም ዕውቀት መሠረታዊና ጥልቅ የእምነት አስተምህሮዎችን እንደሚያካትት ተነጋግረናል። ለሥጋዊ ሕይወታችን ምግብ እንደሚያስ ፈልገን ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያስፈልገናል ሮሜ 10፥17። አንድ ሰው ወደ ሙሉ ክርስቲያናዊ ሕይወት ደረጃ እንዲደርስ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን፥ ያወቀውን እውነት በሥራ ላይ ማዋል አለበት። በዕውቀት እያደግን ስንሄድና ያወቅነውን ነገር በሥራ ላይ እያዋልን ስንሄድ በእምነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ይኖረናል።

በእምነት ማደግ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? በመንፈሳዊ ሕይወት የማደግ፥ በእምነት የመጠንከርና በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን የማወቅ ጥቅሙ ምንድን ነው? የመንፈሳዊ ሕይወት ግቡ በእነዚህ ነገሮች ማደግ ብቻ ነው? በክርስቲያናዊ ሕይወት የመብሰል ግቡ ይህ አይደለም! ሕይወታችን የሚያድገው ከሌሎች ተነጥሎ አይደለም። በጸጋ እንድናድግ (2ጴጥ. 3፥16) የእግዚአብሔር ቃል በሚገባ የሚተረትሩና የሚተረጉሙ ሰዎች እንድንሆንና (2ጢሞ. 2፥16) በእኛ ስላለው ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁን ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር ዝግጁ እንድንሆን ምክር ተሰጥቶናል (1ጴጥ. 3፥15)። ደኅንነትን ያገኘነው በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉ ሰዎችን በተለይም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሕፃናት የሆኑትን እንድናገለግል ነው። እኛ ራሳችን እንዴት እንዳደግን ስለምናውቅና የእግዚአብሔርም ቃል ሌሎችን እንድናገለግል ስለሚያዘን የክርስቶስን አካል ለማገልገል እንነሳሳለን።

በክፍለ ትምህርት 6 ላይ መደበኛ ስላልሆነ ክርስቲያናዊ ምገባ አንዳንድ ሐሳቦችን ተመልክተናል። ሰዎች ብዙ ቁም ነገሮችን የሚማሩት መደበኛ ባልሆነ የማስተማሪያ ሥርዐት ነው፤ በቤትና በጎረቤት ካለን ግንኙነት (ከአብሮነት) ብዙ ትምህርት እናገኛለን፤ ልክ እንዲሁ በመንፈሳዊ ዓለምም

ውስጥ የክርስቶስን ሕይወት የምንማረው የበሰሉ ክርስቲያኖችን ባህርይና ሕይወት በማየት ነው። በመጨረሻም የእኛም ሕይወት ክርስቶስን እየመሰሰ ሲሄድ ሌሎች ሊከተሉት የሚመኙት ሕይወት እንደሚሆን ተነጋግረናል።

አሁን ደግሞ መደበኛ ባሕርይ ስላለው ክርስቲያናዊ ምግባ እንነጋገራለን። በዚህ ትምህርት ደግሞ በክፍል ውስጥ በመሆን በመማር ማስተማር ተግባር የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን እንዴት ማስተማር እንደምትችል ታጠናለህ።

## የማስተማር ተግባር ፍቺ

*ዓላማ 1 የማለተማር ተግባርንና መማር የሀይወት ለውጥን ለምን እንደሚ ያካትት የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

የማስተማር ተግባር ዕውቀትን ማስተላለፍ ብቻ እንዳልሆነ ተመልክተናል። የማስተማር ተግባር ከመናገርና ከማውራት በላይ ነው። ታሪክን መተረክ፥ እውነትን መግለጥ፥ እውነቶችን መተንተንና ዕውቀትን መዘርዘር በራሱ ውጤታማ የማስተማር ተግባር ነው ላይባል ይችላል። ይህ ሁሉ ተደርጎ ሰዎች ምንም ነገር ካልተማሩ የማስተማር ተግባሩ ውጤታማ አልነበረም ማለት ነው። እንዲህ ያለ ነገር ሲያጋጥም ነገሩን በጥሞና መመርመር ያስፈልጋል። አስተማሪው ውጤታማ ሳይሆን የቀረው ደካማ የማስተማሪያ ስልት ስለተጠቀመ ነው? ተማሪዎቹን የሚያስተምረው አንድን የስሜት ህዋስ ብቻ የሙጥኝ በማለት ነው? አለተማሪው ሌሎቹን የስሜት ህዋሳት ለምሳሌ እንደ ማየትና መስማትን ረስቶአቸዋል? የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ሊያዳብር የሚችለውን ለምሳሌ እንደ ውይይት ያለውን የማስተማሪያ ስልት ችላ ብሎአል? «ሸማቹ ካልገዛ፥ ነጋዴው ሸቀጡን አልሸጠም» የሚለው ብሂል የመማር ማስተማር ሂደትን በትክክል ይገልጻል። ለምሳሌ ተማሪው በሚገባ መማር ካልቻለ፥ የማስተማሪያ ስልታችን ትክክለኛ አይደለም ማለት ነው። አንድ ሰው በክፍል ቆሞ ስለተናገረ ብቻ ተማሪዎች ተምረዋል ማለት አይቻልም። መማርና ማስተማር ጥብቅ ትስስር ስላላቸው አንዱ ያለ ሌላው ውጤታማ መሆን አይችልም። እውነት ጣፋጭ ባልሆነ መንገድ መቅረብ የለበትም፤ እንዲሁም እንደ ነገሩ በተማሪው ላይ መወርወር የለበትም። ተማሪ በግድ እንዲማር መደረግ የለበትም። እንግዲህ የማስተማር ተግባር በትክክል ሊከናወን የሚችለው እንዴት ነው?

ቀደም ሲል ያነሳነውን ሐሳብ እዚህ ላይ እንደገና በማንሳት አጽንዖት መስጠት ይኖርብናል። አንድ ተማሪ የሚማረው ነገር ትርጉም እንዲሰጠው ትምህርቱን በግሉ ማጣጣም አለበት፤ ከሚማረው ነገር ውስጥ እውነትን ራሱ ፈልጎ ማግኘት አለበት። ማንም አስተማሪ እንዲህ ሊያደርግለት አይችልም። ይሁንና በአስተማሪው መሪነት እውነትን ማግኘት ይችላል። ስለዚህ በመማር ሂደት ውስጥ አስተማሪ መሪ ሊሆን ይችላል። የማስተማር ተግባር ተማሪዎች ትምህርት እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፤ ተማሪዎች እንዲማሩ መርዳት ነው። ተማሪው የተማረውን ነገር ከዚህ በፊት ከሚያውቀው ነገር ጋር እያስማማ ማጣጣም አለበት። የተማረው ነገር ከእርሱ ጋር እንዴት





እንደሚዛመድ ማስተዋል አለበት፤ እንዲሁም የተረዳውን ነገር ከዕለት ተዕለት ሕይወቱ ጋር ማዛመድና ሕይወቱን አሁን ካገኘው እውነት ጋር ማስተሳሰር አለበት። "በመማር ሂደት ስውጥ እጅግ አስፈላጊ ነው» የሚባለው ለዚህ ነው። እንግዲህ አስተማሪው «የለውጥ ተወካይ» ነው። በሰዎች ሕይወት ውስጥ የአስተሳሰብና የባሕሪ ለውጥ ካየን፥ ሰዎች በእርግጥ ተምረዋል ማለት ነው።

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አስተማሪውም ሆነ ተማሪው ወሳኝ ሚና አላቸው። ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የአስተማሪውና የተማሪው ሚና ምን እንደሆነ እንዲሁም በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ያሳየናል።

እንግዲህ የማስተማር ተግባር፥ ተማሪዎች በሚገባ እንዲማሩ የተመቻቸ ሁኔታን «መፍጠር»፥ ተማሪዎችን «ማበረታታት» እንዲሁም ተማሪዎች እውነትን ራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ «መምራት»ን ያካትታል። የማስተማር ተግባር፥ ተማሪዎች ቁም ነገር እንዲያገኙ የተለያዩ የመማሪያ ስልቶችን ማዋቀር ያካትታል። እንዲሁም ተማሪው የተማረውን ነገር በአግባቡ መመርመር እንዲችል በሚገባ የታቀዱ የቤት ሥራዎችን መስጠትና ተማሪውን ለስውጥ የሚያዘጋጁ ልምዶችን ማካፈልን ያጠቃልላል። ተማሪዎች የተፈለገውን ለውጥ እንዲያመጡ ማስትም ተማሪዎችን አሁን ካሉበት ደረጃ አስተማሪው ወደሚፈልገው ደረጃ ለማምጣት፥ አስተማሪው (1) ተማሪው መማር የሚገባውን ነገር መወሰን አለበት

| የአስተማሪው ኀላፊነት | የተማሪው ኀላፊነት |
|---|---|
| –ተማሪው የሚማረውን ነገር በግሉ እንዲመረምረው ማበረታታት፤ ተማሪው ጠያቂ እንዲሆን ማገዝ፤ የሚያስተም ረውን ትምህርት በሚገባ ማዘጋጀት። | –የተማረውን ነገር በግሉ መመርመር |
| –ተማሪው እውነትን በራሱ ፈልጎ እንዲ ያገኝ መምራት፤ ተማሪው ሊያደርገው የሚገባውን ነገር በግልጽ ማስታወቅ። | –እውነትን በራሱ ፈልጎ ማግኘት |
| –ከሕይወት ጋር የተዛመዱ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ ከሕይወት ጋር የተዛመዱ ምሳሌዎችን መጥቀስ፤ ከሕይወት የተማ ረውን መመስከር። | –የተማረውን እውነት ከሕይወቱ ጋር ማዛመድ |
| –በሚችለው ሁሉ መርዳት፥ ሐሳብ መስጠት፥ ማረም፥ መጸለይ፥ በእግዚአ ብሔር መታመን | –ከተማረው እውነት ጋር ሕይወቱን ማስማማት |

(ይህን ለማወቅ አብዛኛውን ጊዜ ቅድመ ፈተና ይሰጣል)፤ (2) የትምህርቱን ዓላማ መወሰን አለበት፤ (3) ዓላማውን ከግብ የሚያደርሱለትን የቤት ሥራዎች መቅረጽ አለበት፤ (4) ሂደቱን መገምገም አለበት።

መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በመሆኑም ያገኘነውን እውነት እርሱን ደስ በሚያሰኘው መንገድ መኖር አለብን። በሦስተኛ ደረጃ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ መመርመርና ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ጋር እንዴት ልናዛምደው እንደምንችል ልናሰብበት ያስፈልጋል። አራተኛው እንዲህ የመሰለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተማሪው ውስጣዊ ፍላጎቱን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስማማው ወደሚችል ደረጃ ይወስደዋል። እንዲሁም የህይወትን ወሳኝ ገጽታዎች በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት መመርመርና በእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ የተገራን ሕይወት መኖር ወደሚችልበት መንፈሳዊ ልምምድ ይወስደዋል። መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ ባለ መልክ ማጥናትን የምንማረው ከዝቅተኛ ደረጃ በመጀመር ነው፤ በመጀመሪያ መሠረታዊ የሆኑ አስተምህሮዎችን በመማር ከሕይወታችን ጋር እናዛምዳለን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ አዳዲስ ሐሳቦችን ስንማር ትምህርቱ ይበልጥ እየጠለቀና እየሰፋ ይመጣል። ክርስቲያናዊ ሕይወታችን እየበሰለ በሄደ ቁጥር፥ መንፈስ ቅዱስ ከአንድ የእምነት ደረጃ ወደ ሌላ የእምነት ደረጃ ቀስ እያለ ያሸጋግረናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን እውነት መሠረት በማድረግ አንዳንድ ሐሳቦችን ማፍለቅ ከምትችልበት መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ደርሰህ ይሆናል። በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ከመቀበልህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን አንብበው መረዳት የሚችሉት ልዩ ሥልጠና የወሰዱ አገልጋዮች፥ ካህናትና የሃይማኖት መሪዎች ብቻ ናቸው የሚል ነገር ተምረህ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመረዳት የተለየ መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጠው ለእነዚህ ሰዎች ብቻ ነው የሚል አባባል ሰምተህም ይሆናል። ይሁንና እግዚአብሔር ቃሉን መረዳት እንድንችል የሰጠንን መለኮታዊ ስጦታዎች አስታውስ። ዮሐ. 14፥26 እና 16፥13 እንደሚያስገነዝቡን፥ የእግዚአብሔርን እውነት መረዳት እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖችን ሁሉ አንተንም ጨምሮ ይረዳናል፥ ያግዘናል። መጽሐፍ ቅዱስ በሚጻፍበት ወቅት ጸሐፊዎቹን ይመራ የነበረው መለኮታዊ ደራሲ (መንፈስ ቅዱስ) በግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ አንተም እውነትን እንድትረዳ ይመራሃል፥ ያግዝሃል (2ጴጥ. 1፥19–20)። በመንፈሳዊ ሕይወትህ ማደግ ከፈለግህ፥ የእግዚአብሔር ቃል ማጥናት አለብህ። ደግሞም የበሰለ ክርስቲያን ለመሆን ከፈለግህ፥ የተማርኸውን እውነት ከሕይወትህ ጋር ማዛመድ አለብን። ይህን በአንተ ፈንታ ሊያደርግ የሚችል ማንም የለም። እንግዲህ ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ እውነቶችን እንዴት ማግኘት እንደምትችልና ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት እንዲያገኙ እንዴት ልትመራቸው እንደምትችል መማር አለብህ።

(4). ስለግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ለፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ቀደም ብሎ ያልነበረን እውነት መፍጠርን ያጠቃልላል።
ለ. እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የገለጸውን ለመማርና እርሱንም ለመታዘዝ ቃሉን በንቃት የሚመረምርበት ዘዴ ነው።





ሐ. ተማሪው ቀደም ሲል የማያውቀውን እውነት ማግኘትን ያጠቃልላል
መ. የእግዚአብሔርን የተገለጠ እውነት በማወቅ የተወሰነ ነው።
ሠ. አስተማሪ እንዲሆኑ የተጠሩ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት አለባቸው።
ረ. የመጽሐፍ ቅዱስን ያዘት መማርና ሕይወትን ከነዚያ ትምህርቶች ጋር ማስማማትን ያጠቃልላል።
ሰ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖችን ሁሉ የእግዚአብሔርን እውነት እንዲያውቁ ያስችላቸዋል።

## ግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መንገዶች

*ዓላማ 3 ሁለቱን የግኝታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መንገዶች የሚገልጹ ትን ንድፎች በትክክል ለይ።*

ቀደም ባለው ክፍል ግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አራት ደረጃዎች እንዳሉት ተመልክተናል፤ እነዚህን አራት ደረጃዎች ከዚህ እንደሚከተለው ባጭሩ ማቅረብ ይቻላል፦

1. ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚያስፈልገውን ነገር መለየት
2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን መረዳት
3. የተረዳነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ከሕይወታችን ጋር ማዛመድ
4. የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ

በግኝታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ሊረዱን የሚችሉ ሁለት የጥናት መንገዶች አሉ። እነርሱም *ስልትን የተከተለ መንገድና የሕይወት ፍላጎትን የተከተለ መንገድ* ይባላሉ። ስልትን የተከተለውን መንገድ ከዚህ እንደሚከተለው በንድፍ ማስቀመጥ ይቻላል፦




ይህ የአጠናን መንገድ ስልትን የተከተለ የተባለበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት በመልክ በመልክና በሥርዐት በሥርዓት የተደራጁ ስልቶችን ስለሚጠቀም ነው። አንድ መጽሐፍ ወይም ክፍል መርጠህ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ወይም ክፍል ውስጥ የገለጠው እውነት ምን እንደሆነ ታጠናለህ። ከዚያም በጥናትህ ላይ እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ ትጀምራለህ፤

«አንተም እንዲሁ አድርግ» ሲል የተናገረው ቃል ነው (ሉቃ. 10፥37)። ይህ ቃል የሚገኝበበትን ዐውደ ንባብ (ሉቃ. 10፥25–37) በትክክል ካልተረዳን፥ የሕግ አዋቂው ሰው የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለበት ጥያቄ ማቅረቡን አናውቅም። እንዲሁም ኢየሱስ የሕግ አዋቂውን ሰው ጥያቄ ከርኅሩኅ ሳምራዊ ምሳሌ ጋር እንዳዛመደው አናውቅም። ስለዚህ አንድ ሰው ባጋጣሚ ማር. 14፥71 ቢያነብና «መግል» ተፈቅዶለል ቢል (በሉቃ. 10፥37 ላይ «አንተም እንዲሁ አድርግ» ስለሚል)፥ እነዚህ ቃላት የሚገኙበትን ዐውደ ንባብ ለላላወቀ ሊሰት ይችላል። ኢየሱስ በሉቃ. 10፥37 ላይ ለሕግ አዋቂው ሰው «አንተም እንዲሁ አድርግ» ሲለው ስለ መሐላ እያለበ አይደለም፤ አንዳንድ ሰዎች ግን የራሳቸውን ሐሳብ ለማስተናገድ ሲሉ ቅዱሳት መጻሕፍት የማይናገሩትን ነገር ሲናገሩ ይገኛሉ። ከእንዲህ መሰሉ ድርጊት ልንርቅና ይልቁንም የእውነትን ቃል በትክክል ልናስተምር ይገባል (2ጢሞ. 2፥15)።

ሁለተኛው ተግባር የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ከምንኖርበት ሕይወት፥ ባሕልና አካባቢ ጋር የማዛመዱ ተግባር ነው። እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን የእግዚአብሔር እውነት በመጀመሪያ የተጻፈው ለእኛ አለመሆኑን ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም ለመረዳት መሞከር ያለብን፥ መጻሕፍቱ በመጀመሪያ ከተጻፉላቸው ሰዎች አንጻር ነው፤ ራሳችንን በእነርሱ ቦታ ማስቀመጥ አለብን። ለመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ተደራሲዎች ያልተላለፈ ሐሳብ ለእኛም አይተላለፍም። እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ያላስተላለፈውን ሐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዳስተላለፈ አድርገን አዲስና ጥልቅ ፍቺ እየሰጠን ቅዱሳት መጻሕፍትን ብንተረጉም የከፋ ስህተት ውስጥ እንወድቃለን፤ አያሌ ሰዎች የነፈቁት (የስህተት ትምህርት ውስጥ የገቡት) ለዚህ ነገር ተገቢ ትኩረት ባለመስጠታቸው ነው።

(5). ከእውነተኛ ዐረፍተ ነገር ፊት ለፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጻፈው ለእኔና ለአንተ ነው።
ለ. ሥርዓታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የቃሉ የመጀመሪያ መልዕክት ላይ መድረስንና በሕይወታችን በአግባቡ መተግበርን ያጠቃልላል።
ሐ. የመጀመሪያዎቹ ተደራስያን የኖሩበትን ጊዜና መቼት በሚገባ ስንረዳ ለእነርሱ የተነገረውን መልዕክት በሚገባ ለመረዳት ተዘጋጅተናል ማለት ነው።
መ. አስቀድሞ እግዚአብሔር ለማስተላለፍ ያልፈለገውን መልዕክት ዛሬ የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ተደርጎ መወሰድ የለበትም።
ሠ. ሥርዓታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ምንባቡን በቀጥታ መመልከትን፣ የተባለውን መተርጎምንና ከሕይወታችን ጋር ማዛመድን ያካትታል።





## በስርዐታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡ ደረጃዎች

*ዓላማ 5 በስርዐታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ልንከተላቸው የሚ[illegible] ሦስት ደረጃዎች የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

ስርዐታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስደን ክፍሉን በጥንቃቄ እንድንመረምርና ትርጉሙንም እንድንጨብጥ የሚያስችለን ስልት ነው። ይህ ስልት ሦስት መሠረታዊ ደረጃዎች አሉት፤ (1) መመልከት/ምልከታ (2) መተርጎም/ትርጎማ እንዲሁም (3) ማዛመድ ናቸው።

«መመልከት ወይም ምልከታ» ሲባል የምናጠናውን ክፍል መልሰን መላልሰን ማንበብ ማለት ነው። በክፍሉ ውስጥ የተባለውን ነገር በጥንቃቄ መመልከትና ማስተዋል ነው። ምልከታ በምናነበው ክፍል ውስጥ ያሉትን ቃላትና አሰላለፋቸውን እንዲሁም ሰዋሰዋዊ አገባባቸውን ደህና አድርጎ ማስተዋልን ያካትታል።

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች በምታጠናው ክፍል ውስጥ ያለውን እውነት እንድታስተውል ይረዱሃል። የመጽሐፉ ጸሐፊ ማን ነው? መጽሐፉ የተጻፈው ለማን ነው? መጽሐፉ ስለተጻፈላቸው ሰዎች ምን እናውቃለን? መጽሐፉ የተጻፈው መቼ ነው? መጽሐፉን ለመጻፍ ያበቁት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የመጽሐፉ ዐቢይ ወይም ማእከላዊ ሐሳብ ምንድን ነው? ጸሐፊው በጥቅሉ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው? ጸሐፊው ነጥሎ ያስተላለፈው መልእክት ምንድን ነው? ክፍሉን በጥንቃቄ አንብብ፤ ምን እንደተባለም አስተውል።

«መተርጎም ወይም ትርጎማ» ጸሐፊው ለማለት የፈለገው ነገር ምን እንደሆነ ሐሳቡን ማወቅን ያካትታል። ጸሐፊው ለማስተላለፍ የሚፈልገው ሐሳብ ወይም ቁም ነገር አለው። በመጽሐፉ አማካይነት ለማስተላለፍ የሚፈልገውን ሐሳብ ወይም ቁም ነገር ለአንባቢዎቹ ያስተላልፋል። አንድ ሐሳብ ወይም ቁም ነገር ከጸሐፊው ወደ አንባቢዎቹ የሚተላለፈው በቃላት አማካይነት ነው። አንባቢዎቹ ለመረዳት መሞከር ያለባቸው የጸሐፊውን ሐሳብ ነው። አንድ በጽሑፍ የሰፈረን ሐሳብ በሚገባ ለመረዳት፥ በትክክል መተርጎም አለበት። እንግዲህ መተርጎም ወይም ትርጎማ ሲባል፥ ጸሐፊው በጽሑፍ ያስተላለፈው ሐሳብ ትርጉሙ ወይም ፍቺው ምን እንደሆነ መወሰንና መለየት ማለት ነው።

እነዚህ ሁለት ደረጃዎች ማለትም መመልከትና መተርጎም የመጀመሪያውን ተግባር እንድናከናውን ይረዱናል። ቀደም ሲል እንደተነጋገርነው ይህ የመጀመሪያው ተግባር መልእክቱ (የምናጠናው ክፍል ወይም መጽሐፍ ) ለመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች የሚሰጠው ትርጉም ምን እንደሆነ በትክክል ማወቅ ነው። ይሁንና ሥራው እዚህ ላይ ብቻ አያበቃም። እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል የተናገረው መጻሕፍቱ ለተጻፈላቸው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ነው። በ2ጢሞ. 3፥16–

በመጠየቅ ነው። የትምህርቱ ዓላማ ላይ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ የሚጨብጡት ዕውቀት ምን እንደሆነ በግልጽ መጠቀስ አለበት። በተማሪዎቹ ላይ ሊታይ የሚገባው ለውጥ ምን አንደሆነ በክፍለ ትምህርት 4 ላይ ተነጋግረናል፤ አነርሱም የዕውቀት፥ የባሕሪና የአስተሳሰብ ለውጥ ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእያንዳንዱን ትምህርት ዓላማ በግልጽ ጠቅሰናል። ይህም አንተ የምታስተምረውን ትምህርት ዓላማ እንዴት ልትቀርጽ እንደምትችል ምሳሌ ስለሚሆንህ በሚገባ አጥናቸው።

በተማሪዎችህ ላይ ልታየው የምትፈልገውን ለውጥ በግልጽ ከወሰንህ፥ አሁን እንዚህ ለውጦች የሚመጡበትን መንገድ ለመንደፍ ዝግጁ ነህ። አሁን የቀረህ ሥራ ተማሪውን ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ አንተ ወዳሰብከው ደረጃ መውሰድ ነው፤ ይህ ደረጃ ምን እንደሆነ በምታስተምረው ትምህርት ዓላማ ላይ ተገልጾአል። እዚህ ላይ ተገቢ የማስተማሪያ ስልቶችን መምረጥ አለብህ፤ ተማሪው የሚሠራቸውን የቤት ሥራዎች በሚገባ ማቀድና በተማሪው ላይ ለማየት የምትፈልገውን ለውጥ ለማምጣት ያለህን ጊዜ እንዴት መጠቀም እንዳለብህ መወሰን ይኖርብሃል። እንዚህ ሁሉ ነገሮች ተማሪው ከሚማረው ትምህርት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቅ ሊያደርጉት ይገባል። እንዲሁም ከተማረው እውነት ለሕይወቱ የሚጠቅመውን ነገር ለመውሰድ የሚያስችሉት መሆን አለባቸው።

የመማር ማስተማር ግብ ሰዎች ትምህርት እንዲገበዩ ማድረግ በመሆኑ፥ ትምህርቱን ለማስተማር የምንጠቀምባቸው ስልቶች አስተማሪው በሚያደርገው ነገር ላይ ሳይሆን አጽንዖት መበጠት ያለባቸው ተማሪዎቹ በሚያደርጉት ነገር ላይ ነው። ይህ መቼም ልንዘነጋው የማይገባ መርህ መሆን አለበት፤ ተማሪው ከሚማረው ትምህርት ጋር የመታገል ልምድ ሊያዳብር ይገባል፤ እንዲሁም የሚማረውን ትምህርት በራሱ የመመርመርና የመፈተሽ ፍላጎት ሊያዳብር ያስፈልጋል። ተማሪውን ለማስተማር የምንነድፈው ተግባር፥ ተማሪው የተማረውን ነገር በራሱ የሚመሬምርበትን ዕድል ያካተተ መሆን አለበት።

የመጨረሻው ደረጃ የተማሪውን ዕድገት መገምገም ነው። የተማሪውን ዕድገት ወይም ተማሪው የደረሰበትን ደረጃ ለመገምገም፥ ተማሪው አሁን የደረሰበትን ደረጃ ወይም ያሳየውን ዕድገት ተማሪው እንዲደርስበት አስበነው ከነበረው ደረጃ ጋር ማነጻጸር ይቻላል። ተማሪው እንዲደርስበት የምንፈልገው ደረጃ በትምህርቱ ዓላማ ላይ ተገልጾአል። በለዚህ የተማሪውን ደረጃ በትምህርቱ ዓላማ ላይ ተገልጾአል። ስለዚህ የተማሪውን ደረጃ የምንገመግመው በትምህርቱ ዓላማ መሠረት ነው ማለት ነው። ተማሪው የታሰበውን ለውጥ አምጥቶአል? እንዲያመጣ የታሰበውን ለውጥ እስከምን ድረስ አሳይቶአል?

ተማሪው የታሰበውን ለውጥ ማምጣቱን የምንለካበት በርካታ መንገዶች አሉ። አንደኛውና በጣም የተለመደው መንገድ ተማሪውን መፈተን ነው። የፈተና ወይም የጥያቄ ዐይነቶች ብዙ ናቸው። «ምርጫ» ያላቸውን ጥያቄዎች በመስጠት፥ እውነት ወይም ሐሰት እያለ እንዲመልስና በአንድ ወገን ያሉ





ጥያቄዎችን በሌላ ወገን ካሉ መልሶች ጋር እንዲያዛምድ በማድረግ የተማሪውን ደረጃ ማወቅ ይቻላል። እንዲሁም በአጭርና በረጅም ጽሑፍ የሚብራሩ ጥያቄዎችን በመስጠት ምን ያህል እንደተማረ መገምገም ይቻላል።

የተማሪዎችን ደረጃ የምንገመግምበት ሌላው መንገድ የተማሪዎቹን ባሕርይ በቅርብ በመከታተል ነው። ተማሪዎቹ የተማሩትን ነገር ከሕይወታቸው ጋር አያዛመዱትና እያስማሙት መሆኑን ቀረብ ብሎ መመልከት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ለተማሪዎቹ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ የደረሱበትን ደረጃ ማወቅ ይቻላል። ከተማሪው ጋር ስትነጋገር ያሳየውን ዕድገትና ለውጥ በቀላሉ ማጤን ትችላለህ።

(11). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የማንኛውም የመማር ልምምድ ቀዳሚ ትኩረት ተማሪው የሚፈል ገው ነገር መሆን አለበት።
ለ. ውጤታማ የመማር ልምምድ እንዲኖር የተማሪው ፍላጎትና እንዲያ መጣ የሚፈለገውን ለውጥ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።
ሐ. የትምህርት ዓላማዎች ተማሪዎች እንዲያመጡት የምንፈልገውን ለውጥ ያስገኝ ዘንድ የሚችል የትምህርት እንቅስቃሴ ለማቀድ ይረዳናል።
መ. የትምህርት ዓላማዎች የተፈለገው ለውጥ መምጣቱን ለመመዘን መንገድ ይሆኑናል።
ሠ. የመማር ሂደት በባህሪው የሚጠናውን ትምህርት ይዘት ከመበማትና ከመረዳት ያለፈ ነገር ከተማሪው አይጠይቅም።

(12). የትምህርት እንቅስቃሴ ሲታቀድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው

ሀ. አስተማሪው የሚከተለው ቅደም ተከተልና የሚያደርገው ነገር
ለ. እንቅስቃሴዎቹ የሚወስዱት የጊዜ መጠንና ከተሰጠው የትምህርት ጊዜ ጋር መጣጣማቸው
ሐ. ተማሪው የሚያደርገው ነገርና ከትምህርቱ ጋር ያለው መስተጋብር

(13). በትምህርቱ መሠረት የተማሪዎችን እድገት ልንመዝን የምንችል በት መንገድ

ሀ. የተበጣቸውን የትምህርት ይዘት ቃል በቃል መያዛቸውን ፈትኖ በማየት
ለ. የተማሪውን እድገት እንዲመጣ ከታሰበው እድገት ጋር በማወዳደር
ሐ. ከትምህርቱ በፊት ተማሪዎች የነበሩበትን ሁኔታ አሁን ከመጣ እድገት ጋር በማነጻጸር
መ. የተማሪዎችን ሁኔታ በሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ውስጥ ከተሰጠው የክርስቲያን ሕይወት ሞዴል ጋር በማነጻጸር

12. ሐ

6. ለ

13. "ለ" እና "ሐ"





# 8 በቤተሰብ ውስጥ ማደግ

## ትምህርት

አንድ ቀን ወደ ቀትር ላይ ግርማ የተበላሸችበትን መኪና ይጠግናል። አጠገቡ አማኑኤል አለ፤ አማኑኤል አባቱ ግርማ የሚያደርገውን ሁሉ በቅርብ ሆኖ ይከታተላል። ግርማ የተበላሸችበትን መኪና ይጠግንበት የነበረው መፍቻ አምልጦት እጁን ሲመታው በጣም አመመውና ጮኸ። በማግሥቱ አማኑኤል በጫወታ ላይ እያለ፥ አባቱ ሲጠቀምበት ባየው መፍቻ ብስኪሌቱ እንደተበላሸችበት ሰው በመምሰል ይጠግናል። አማኑኤል ሲጫወት ፀሐይ ልብ ብላ ትከታተለዋለች፤ አማኑኤል ቢሲኪሌቱን የሚጠግንበት መፍቻ ከእጁ አምልጦት ወደቀ። በዚህ ጊዜ ትላንት አባቱ ሲጮኸ የተጠቀመበትን ቃል እርሱም ሲጠቀምበት ሰማች።

በዚያን ምሽት ፀሐይ በአማኑኤል ላይ ያስተዋለችውን ሁሉ ለግርማ ነገረችው። በልጃቸው ሕይወት ላይ ሁለቱም ያላቸውን ኀላፊነት ተወያዩ። አማኑኤል በመልካም ሥነ ምግባር የተገነባና ኀላፊነት የሚሰማው ሰው እንዲሆን ስለሚፈልጉ፥ በልጃቸው ፊት መልካም ምሳሌ ያለው ሕይወት እንዲኖሩ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው አብረው ጸለዩ።

ምናልባት አንተም እንዲህ ያለ ነገር በቤተሰብህ ውስጥ ገጥሞህ ይሆናል። ከወላጆችህ አንዱ ሲያደርጉ ያየኸውን ነገር አንተም ለማድረግ የሞከርህበት ጊዜ ትዝ ይልሃል? ወይም ደግሞ ከልጆችህ አንዱ አንተ የምታደርገውን ነገር ቀድቶ ሲያደርግ አይተህ ይሆናል። ይህ ትምህርት የሚያተኩረው በቤተሰብ ውስጥ ሲኖር ስለሚገባው ሕይወት ነው። የምገባ ዓላማ (ለዎችን የእግዚአብሔርን ቃል የምንመግብበት ዓላማ) ለዎች ሙሉ የሆነ ሕይወት እንዲኖራቸውና ክርስቶስን ወደ መምሰል እንዲያድጉ ነው። በቤተሰብ ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ከምንም በላይ የላቀ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ቤተሰብ የሚናገረው ብዙ ነገር አለ። በተለያዩ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች አማካይነት የክርስቶስን አካል ስታንጽ ይህ እውነት (ማለትም ቤተሰብ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ትልቅ ቦታ እንደተሰጠው) ደምቆ እንዲታይህ ምኞታችን ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚያስተምረው
- የቤተሰብ መሠረታዊ ጠባይ

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ።

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚናገረውን ነገር በዝርዝር ማብራራት ትችላለህ።
- ጋብቻ እንዲያድግና እንዲጠነከር እንዴት መርዳት እንደሚቻል መናገር ትችላለህ።
- ሁለቱን የክርስቲያን ወላጆች ተግባር መግለጽ ትችላለህ።
- ቤተሰባዊ ሕይወት እንዲያድግ የሚረዱት ሁለት ነገሮች ምን እንደሆኑ ማብራራት ትችላለህ።

---

## የትምህርቱ ዝርዝር

# *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚያስተምረው*

### እግዚአብሔር ጋብቻን እንዴት እንደመሠረተ

*ዓላማ 1 እግዚአብሔር ሰውን ለምን እንደፈጠረ፥ ሰው ከሌሎች ፍጥረታት እንዴት እንደሚለይ፥ ሴትን ለምን እንደተፈጠረ፥ ጋብቻ እርስ በርስ መደጋገፍ እንደሆነና እግዚአብሔር ቤተሰብን አንድ ተቋም አድርጎ የመሠረተው ለምን እንደሆነ በሚገባ ለይ።*

የዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች እግዚአብሔር ለለሠራቸው ድንቅ ሥራዎች ይናገራሉ። በእነዚህ ምዕራፎች ላይ ስለ ሰማይና ስለ ምድር አፈጣጠር በዝርዝር ተገልጾአል። እግዚአብሔር ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን በየቦታቸው እንዳስቀመጠ ተነግሮአል። ምድርን ደግሞ ውብና አስደናቂ በሆኑ የተለያዩ እጽዋት እንደሞላ ተጽፎአል፤ እነዚህ እጽዋት መራባት የሚችሉና ራሳቸውን መተካት የሚችሉ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ምድርን፥ ባሕርንና ሰማይን በልዩ ልዩ አስደናቂ ፍጥረታት እንደሞላና የፍጥረት ሥራውን ከፍጻሜ ሲያደርስ እንደተቃረበ እንመለከታለን። ከዚያም የሠራውን ሁሉ ምለስ ብሎ ሲመለከት ሁሉም መልካም እንደሆነ አየ።

እግዚአብሔር በመጨረሻ የፈጠረው የፍጥረቱ ሁሉ ቁንጮ የሆነውን የሰውን ልጅ ነው። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በራሱ መልክ ነው። እግዚአብሔር ከሰው በስተቀር በራሱ መልክ የፈጠረው አንድም ፍጥረት የለም። ሰውን ከምድር ዐፈር ከሠራ በኋላ በአፍንጫው የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት። ይህ በእግዚአብሔር መልክ የተሰራው ፍጥረት ሰው ነው። እርሱም ከሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ ልዩ ነው፤ ምክንያቱም ሰው ምግባራዊ ፍጡር ነው። በመልካምና በክፉ መካከል ምርጫ የማድረግ ችሎታ አለው። ሰው ከፈጣሪው





ጋር የሚመሳሰለው በዚህ ችሎታው ነው። ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ይችላል።

ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው ምግባራዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን «ብቸኛው» በመሆኑ ጭምር ነው። ሌሎች ፍጥረታት የተፈጠሩት ጥንድ ጥንድ ሆነው ነው፤ ማለትም ወንድና ሴት ሆነው ነው። ሰው ግን በኤደን ገነት ውስጥ ብቻውን ይሠራ ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦ «ሰው ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም፤ ስለዚህ ተለማሚና ረዳት ጓደኛ እፈጥርለታሁ» (ዘፍ. 2፥18)። ከዚያም እግዚአብሔር ከአዳም ጎን አጥንት ወስዶ ረዳት ጓደኛ እንድትሆነው ሴትን ፈጠረ። ሴት የተፈጠረችው የአዳም ረዳት ጓደኛ በመሆን ገነትን አብረው ለመጠበቅ ነው፤ የአዳምን ኀላፊነት ለመካፈል ነው። የባሏን ድካም በመሙላትና ለባሏ ጓደኛ በመሆን ከባሏ ጋር ምድርን ለመሙላት ነው።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በልዩ መንገድና ለተለየ ዓላማ ነው። ሰው የተፈጠረው ለእግዚአብሔር ፍቅር ምላሽ እንዲሰጥና እግዚአብሔርን እንዲያከብር ነው። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር ሰውን ጥንድ አድርጎ የፈጠረው የተለየ ኅብረት በመካከላቸው እንዲኖር ነው። የባልና የሚስት ግንኙነት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ መኖር የሚገባው መሠረታዊ ግንኙነት ሲሆን ይህ ግንኙነት ማኅበራዊ ጠባይ የሚታይበት ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለሴት፥ ሴትን የፈጠረው ደግሞ ለሰው በመሆኑ፥ ቤተሰብን የመሠረተው እግዚአብሔር እንደሆነ እንመለከታለን።

በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እንደምናነበው የባልና የሚስጥ ግንኙነት የመረዳዳትና የመደጋገፍ ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ሲያደርግ፥ አንዱ የሌላውን ፍላጎት እንዲሞላ ነው። እርስ በርስ ኅብረት የማድረግ ችሎታ ያላቸው ሲሆን፥ አንዱ የሌላውን ስሜታዊ፥ አእምሮአዊና መንፈሳዊ ገጠመኝ መካፈል ይችላል። ከዚህም በላይ ጋብቻ በሁለት የትዳር ጓደኞች መካከል እጅግ ጥብቅ የሆነ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል። እግዚአብሔር ይህን አንድነት ከባረከ በኋላ እንዲበዙና እንዲባዙ፥ ምድርንም እንዲሞሉ አደረጋቸው።

እንግዲህ እዚህ ላይ እንደምናየው፥ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን የፈጠረው ምድርን እንዲጠብቁና አንዳቸው የሌላውን ፍላጎት እንዲሞሉ ብቻ ሳይሆን ልጅም እንዲወልዱ ጭምር ነው። ልጅ መውለድና ማሳደግ ለሰው ልጆች የተሰጠ አንዱ ስጦታ ነው። አዳምና ሔዋን በመካከላቸው እንዲኖር የተደረገውን የእርስ በርስ ግንኙነት አብረው እንዲካፈሉ ቢደረጉም፥ ከልጆቻቸውም ጋር ፍቅርን መሠረት ያደረገ ግንኙነት እንዲፈጥሩም ተደርጎአል። ወላጅ እንደ መሆናቸው መጠን ልጆቻቸው እግዚአብሔርን እየፈሩና እያከበሩ ማደግ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። ሕይወታቸውና ትምህርታቸው ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና ታማኝነት የሚገልጽ መሆን አለበት። በዚህ ዐይነት ልጆቻቸው በፊታቸው የተቀመጠውን መልካም ምሳሌ እያዩ ያድጋሉ። ልጆቹ ወደ ሙሉ የጎልማሳነት ሕይወት

በማደግ እነርሱም የራሳቸውን ቤተሰብ መሥርተው ልጆቻቸውን የእነርሱ ወላጆች ባስቀመጡላቸው ሕይወት መሠረት ማሳደግ ይጀምራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው፥ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ምገባ (ሕይወትን መመገብና መኮትኮት) በባልና በሚስት እንዲሁም በወላጆችና በልጆች ግንኙነት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። እንዲሁም ምገባ በቤተሰብ ውስጥ እንዲኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ በግልጽ ያስተምራል። የቤተሰብ ሕይወት ምን መልክ ሊይዝ እንደሚገባ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተብራርቶ ተጠቅሶአል። የቤተሰብ ሕይወት ሊኖረው የሚገባው መልክ በምሳሌ 22፥6 ላይ በግሩም ሁኔታ ተጠቃሎአል፦ «ልጅን እንዴት መኖር እንደሚገባው ብታስተምረው፥ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ከዚያ ፈቀቅ አይልም»። ከዚህ ቃል የምንረዳው እግዚአብሔር ቤተሰብን የመሠረተው ሰዎች ሙሉና የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያውቁ ሆነው እንዲያድጉና እንዲበስሉ ነው፤ ይህ የሚሆነው ደግሞ በምገባ ነው።

1-5 ቀደም ባለው ትምህርት ላይ በመመሥረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ።

(1). ሰውን በመፍጠሩ የእግዚአብሔር ዓላማ

ሀ. ለፍጡሩ ተንከባካቢ ለማዘጋጀት
ለ. ምሪቱን የሚቀበልና እርሱን የሚያከብር እንዲሆን
ሐ. የዓለምን ሕዝብ ብዙ ለማድረግ

(2). ሰው ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የሚለይበት መንገድ፡

ሀ. ከሌላው ፍጥረት ሁሉ በተለየ ማሰብ መቻሉ
ለ. በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ
ሐ. ውስብስብ ፍጥረት በመሆኑ ብቻ ከሌላው ፍጥረት ይለያል።

(3). ከሚከተሉት አንዱ ሴት የተፈጠረችበትን ምክንያት አያገልጽም።

ሀ. የሰው ረዳት እንድትሆን ተፈጠረች።
ለ. ከሰው ችሎታ ጋር በአጋርነት እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለው ዕቅድ እንዲፈጸም።
ሐ. በፍጥረት ውስጥ የተገዢነትና የበታችነት ሥፍራ እንድትይዝ።
መ. በምገባና በምሳሌነት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆች እንድታሳድግና የሰው ዘር እንዲቀጥል።

(4). በጋብቻ ውስጥ ያለው የረዳትነት አሳቤ

ሀ. ሴት የወንድ ተገዢ መሆኗን አመልካች ነው።
ለ. ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ፍላጎት ሲያሟሉ የእግዚአብሔር ዓላማ በዚያ ግንኙነት ውስጥ ይፈጸማል።





ሐ. አንዱ የትዳር ጓደኛ የሌላው ፍላጎት ላይ ሲያተኩር የእያንዳንዱ ፍላጎት ይሟላል።

(5). የእግዚአብሔር ቤተሰብን የመፍጠር ዕቅድ ውስጥ ዓላማውን በተሻለ የሚገልጸው መልስ የትኛው ነው?

ሀ. ሰው ምድርን ሲሞላትና ሲንከባከባት የመመገብ ግንኙነት እንዲኖር።
ለ. ምድርን መሙላት፣ በፍሬዋ መደሰትና እርሷንም መንከባከብ።
ሐ. ለፈጠረው ሕዝብ ማኅበራዊ ሥርዓትንና መንግሥትን ለማቆም።

## የጋብቻ መሠረታዊ ጠባይ

*ዓላማ 2 በዚህ ትምህርት ውስጥ መመገብ፥ መከባከብ፥ መውደድ፥ የቅርብ ግንኙነትና አንድነት ለሚሉት ቃላት የተሰጠውን ትርጉም ከቃላቱ ጋር አዛምድ።*

የጋብቻ ግንኙነት እጅግ ልዩ በመሆኑ በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ጋብቻ ልዩ ክብር አለው። አብዛኛውን ጊዜ ጋብቻ የሚመሠረተው በመንግሥት ወይም በሃይማኖታዊ ተቋማት ወይም በአገር ወግና ልማድ መሠረት ነው። ይህም አንድ ወንድና አንድ ሴት ቤተሰብ መመሥረታቸውን ወይም ባልና ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ነው።

የአንድ ወንድና የአንድ ሴት ጋብቻ በመካከላቸው ባለ መቀባበልና መተሳሰር ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ባል ራሱን ለሚስት ይሰጣል፤ ሚስትም ራሷን ለባል ትሰጣለች። ዘፍ. 1፥26-28 እና 2፥20-25 ብጥምና ብንመረምር የአንድ ጋብቻ ባሕርያት ምን እንደሆኑ በግልጽ እንረዳለን።

1. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የሚመሠረት ግንኙነት ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር የተደነገገ ነው። እግዚአብሔር ሁለቱንም ልዩ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል። ስለዚህም አንዱ ለሌላው ያስፈልጋል።

2. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የሚመሠረት «አንድነት» ነው፤ ይህ አንድነት ጥብቅ በሆነ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን እግዚአብሔር ሁለቱን አንድ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ለዚሁ ዓላማ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እግዚአብሔር ሴትን የፈጠረው ከአዳም ጎን በወሰደው አጥንት ነው። ይህም በጋብቻ ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው አንድነት ትልቅ ምሳሌ ነው። አዳም ሔዋንን ያያት የአካሉ ክፋይ አድርጎ ነው። እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠረው በወሰደው አጥንት ቢሆንም ለሔዋን የሰጠው ቅርጽ ለአዳም ከሰጠው ቅርጽ የተለየ ነው። ይህ በሁለቱ መካከል ያለው የቅርጽ ልዩነት እርስ በርስ እንዲፈላለጉና የቅርብ ግንኙነትም እንዲመሠርቱ ያደርጋቸዋል።

3. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ብቻ የሚመሠረት ግንኙነት ነው። በሌላ አነጋገር የአሀዳዊ ጋብቻ ግንኙነት ነው። በብዙ ኅብረተሰቦች

### የክፍሉ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ።

- የአነስተኛ ቡድኖች ዓላማ ምን እንደሆነ መግለጽ ትችላለህ።
- በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች የሚያገኙአቸውን አራት ጥቅሞች መናገር ትችላለህ።
- የአነስተኛ ቡድኖችን ውጤታማ የሚያደርጉ ነገሮች ምን እንደሆኑ መግለጽ ትችላለህ።
- አነስተኛ ቡድኖችን እንዴት ማደራጀትና መምራት እንደሚቻል መለየት ትችላለህ።

---

### የክፍሉ ትምህርቱ ዝርዝር

## በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የክርስቶስን ሕይወት መካፈል

### የአነስተኛ ቡድኖች (ህብረቶች) ዓላማ

*ዓላማ 1 የአነስተኛ ቡድኖች ዓላማ ምን እንደሆነ የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ የጋራ ነገር አላቸው፤ ሁሉም አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ወይም የኢየሱስን ሕይወት ተቀብለዋል። ይህን ትምህርት በምታጠናበት ጊዜ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ከፈለገ መንፈሳዊ ሕይወቱን መመገብ እንዳለበት ተረድተሃል። አሁን ደግሞ ለመንፈሳዊ ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርጉትን ሌሎች ነገሮች ትማራለህ። እኛ ክርስቲያኖች የኢየሱስን ሕይወት ስለምንጋራ (ስለምንካፈል) እርስ በርስ የተያያዝን ነን። ይህን የኢየሱስን ሕይወት የተጋሩ (የተካፈሉ) ሁሉ የእርሱ አካል ክፍል ናቸው (1ቆሮ. 12፥12–27)። ይህም ማለት ክርስቲያኖች ሁሉ እርስ በርስ ሕያው በሆነ መንገድ ተያይዘዋል ወይም ተጋጥመዋል ማለት ነው። ይህ የእርስ በርስ መያያዝ ወይም መጋጠም እያደገ ካልሄደ ትርጉም የለሽ ይሆናል፤ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አካል ያድጋል፤ ያብባል። ይህ በክርስቶስ ያገኘነው አንድነትም ማደግና ማበብ አለበት።

የእያንዳንዳችንን ሕይወት የማሳደግ ኀላፊነት እንዳለብን ሁሉ በኅብረት አብረን የማደግ ኀላፊነትም አለብን። ቤተክርስቲያን ብርቱና ፍሬያማ መሆን የምትችለው እያንዳንዱ አባል ሲያድግና ሲበስል ነው። እያንዳንዱ የአካል ክፍል አካሉን ለማሳደግ የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል፤ በዚህ ዐይነት አካሉ በሙሉ ያድጋል። በየራሳችን ሰውነት ላይ እንደምናየው እያንዳንዱ የአካል ክፍል የየራሱን ድርሻ ሲፈጽም አካሉ ጤናማና ፍሬያማ ሆኖ ያድጋል። ልክ





እንዲሁ የክርስቶስ አካል ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት የሚችለው እያንዳንዱ አባል የበኩሉን ድርሻ ሲፈጽም ነው። እያንዳንዱ አባል የበኩሉን ድርሻ እንዲፈጽም አነስተኛ ቡድኖች ዐይነተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። የአነስተኛ ቡድኖች አባላት ያላቸውን ነገር ሁሉ ወደ ቡድኑ ሲያመጡ ይህ ለቡድኑ አባላት ምን ጥቅም እንደሚያመጣ እንመለከታለን። አነስተኛ ቡድኖች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ወደፊት ያራምዳሉ፤ እግዚአብሔር የሚከበርበትን፥ መንግሥቱ የሚሰፋበት ትንና ሕዝቡ የሚታነጽበትን ነገር ያበረክታሉ። እንግዲህ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ሕይወት ለመካፈልና አንዱ ለሌላው በረከት ለመሆን ኅብረት ማድረግ አለባቸው።

መንፈሳዊ ሕይወትን ለማሳደግ ከሚጠቅሙት ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው አነስተኛ ቡድኖች ናቸው። ከ10–12 ሰዎችን የሚያሳትፉ አነስተኛ ቡድኖችን በማቋቋም የምልጃ ጸሎት ማድረግ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና መንፈሳዊ ጉዳዮችን መከፋፈል ይቻላል። እንዲህ ያሉ ቡድኖች መንፈሳዊ ሕይወትን ለማሳደግ እጅግ ምቹ ስፍራዎች ናቸው። እንዲህ በመሳሰሉ ቡድኖች ውስጥ የሚደረጀው ግንኙነት የክርስቶስን ሕይወት እርስ በርስ ለመካፈልና በመንፈሳዊ ሕይወት እድገና ጎልምሶ ለመገኘት እጅግ ጠቃሚ ናቸው። በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ የሚፈጠረው ግንኙነት እያንዳንዱ አባል ከሌሎች ሰዎች የሚሻውን መንፈሳዊ ምክርና ምግብ እንዲያገኝና እርሱም ለሌሎች የሚያበረክተውን መንፈሳዊ ምክርና ምግብ አብሮ ለመካፈል ትልቅ ዕድል ይሰጣል። የአነስተኛ ቡድኖች አባላት እያንዳንዱ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ የሚያስፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ስለሚያውቁ፥ የቡድኑ አባላት መንፈሳዊ ሕይወት እርስ በርስ ባላቸው ትውውቅና ትስስብ ያድጋል።

እንዲህ ያሉ ኅብረቶችና የእርስ በርስ ግንኙነቶች እንዲሁም አንዱ ለሌላው የሚያሳየው ፍቅርና የክርስቶስን ሕይወት በጋራ ለመካፈል የሚያደርጉት ጥረት የቤተክርስቲያን መለያና መታወቂያ ናቸው። በቤተክርስቲያን ውስጥ እነዚህ ነገሮች እንዲታዩ ክርስቶስ ይፈልጋል። እነዚህ ነገሮች በማይታዩባት ቤተክርስቲያን ክርስቶስ ብዙ አይደሰትም። አካሉን ለማሳደግ የቤተክርስቲያን ራስና ጌታ የሆነው ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ልዩ ልዩ የአገልግሎት ስጦታዎችን ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል፤ ክርስቶስ እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች ለቤተክርስቲያን የሰጠው በአካሉ ውስጥ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲዳብርና አንዱ ሌላውን እያገለገለ በአንድነት እንዲያድጉ ነው።

1-5 ከዚህ በላይ በተሰጠው ትምህርት መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች የትክክለኛውን መልስ ፊደል በመክበብ አመልክት።

(1). በአማኞች መካከል የአነስተኛ ቡድኖች ተቀዳሚ ዓላማ

*ሀ.* በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ያላቸውን አሳብ ለመለዋወጥ።
ለ. የክርስቶስ አካል አንዱ ክፍል ለመሆን።
ሐ. የክርስቶስን ሕይወት በጣም በተቀራረበ ደረጃ ከሌሎች ጋር ለመካፈል።
መ. ኢየሱስ የሰጠንን አዲስ ሕይወት ለመቀበል።

(2). የአማኞች አነስተኛ ቡድኖች ባህሪ

ሀ. እኩል ምድራዊ ሐብት እንዲኖር ይፈልጋል።
ለ. እርስ በእርስ አንዱ ለሌላው አባል ደኅንነት ያስባል።
ሐ. የአንዱን ችግር ሌላው አባል በማየት ያዝንለታል።
መ. በአንድ ዓይነት ችግር ውስጥ ያልፋሉ።

(3). በአማኞች አነስተኛ ቡድን ውስጥ የሚኖረው ግንኙነት ለተካፋዩ ግለሰብ የሚያስገኝለት

ሀ. እርስ በእርስ በመበረታታት ለመንፈሳዊ ዕድገት መንገድ ይከፍታል።
ለ. እግዚአብሔርን ስለመምሰል ሕይወት የማወዳደሪያ መሠረት ይሰጠዋል።
ሐ. ከዓለም ጋር እንዳይገናኝ ይረዳዋል።
መ. እያንዳንዱ ስለ እምነቱ ለቡድኑ እንዲመሰክር ያስችለዋል።

(4). ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያኑ መለያ ምልክት እንዲሆን የፈለገው ነገር

ሀ. የተቀራረበ ህብረትና ጥሩ የእርስ በርስ ግንኙነት።
ለ. ምድራዊ ኃብትን ሁሉ መተውና መንፈሳዊ ካልሆኑ ነገሮች ሁሉ መለየት።
ሐ. ከሌሎች ሰዎች ተገልሎ መኖርና በርካታ መልካም ሥራዎችን መሥራት።
መ. ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች መለየትና ደካማ ክርስቲያኖች፣ መንቀፍ።

(5). ኢየሱስ የአገልግሎት ሥጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው
ሀ. እያንዳንዱ አባል ትርጉም ያለው ተግባር እንዲሠራ።
ለ. በዝፉው ዓለም ውስጥ ሰዎች በሕይወት እንዲቆዩ ለማድረግ።
ሐ. ክርስቲያኖች ስለ ዓለማዊ ነገሮች በማሰብ ሥራ እንዲበዛባቸው።
መ. እርስ በእርስ ህብረት እንዲኖርና ለምገባ አመቺ እንዲሆን።

## አነስተኛ ቡድኖች በታሪክ ውስጥ

*ዓላማ 2 በክርስትና ታሪክ ውስጥ አነስተኛ ቡድኖች እንዴት ጥቅም ይሰጡ እንደነበር የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

የክርስቲያኖች የክርስቶስን ሕይወት እርስ በርስ ለመካፈል በአነስተኛ ቡድኖች መሰባሰብ አዲስ ነገር አይደለም። በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የእርስ በርስ መተሳሰብና መተሳሰር እንዳለ ኢየሱስ ያውቅ ስለነበር እንደዚህ ያሉ ቡድኖች እንዲኖሩ ፈቃዱ ነበር። ኢየሱስ ከበርካታ ተከታዮቹ ውስጥ ዐሥራ ሁለት ሰዎችን መረጠ፤ ከእነዚህ ዐሥራ ሁለት ሰዎች መካከል ደግሞ ጥቂት ሰዎችን መረጠ። በኢየሱስና በዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መካከል የነበረው ኅብረትና ግንኙነት መተሳሰብና መተጋገዝ የሚታይበት ነበር። በዚህ ዐይነት አንዱ ለሌላው የሚያስፈልገውን በማድረግ አብረው ያድጉ ነበር ከዚህ በተጨማሪ ቡድኑ ራሱ በዓላማና በዕውቀት ኢየሱስ በሚፈልገው መንገድ





ያድግ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ወንጌልን እንዲሰብኩ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ላካቸው፤

የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን አነስተኛ ቡድኖች በአገልግሎታቸው ውስጥ ይጠቀሙባቸው ነበር። ክርስትና ሥር እየሰደደና እየጎለበተ በመጣባቸው የመጀመሪያዎቹ ምዕተ ዓመታት ውስጥ እንደዚህ ያሉ አነስተኛ ቡድኖች እንደነበሩ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ያረጋግጣል። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለመስበክ፥ ለመማር፥ ኅብረት ለማድረግ፥ ለማምለክና ለመጸለይ ይሰበሰቡ እንደነበር በሐዋ. 2፥41–42 ላይ ተገልጾአል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ክፍሎች እንደሚጠቁሙት፥ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በየጊዜው ይሰበሰቡ የነበረው በተለያዩ ክርስቲያኖች ቤት ውስጥ ነበር። እነዚህ ስብሰባዎች እርስ በርስ ለመገናኘት፥ መጽሐፍ ቅዱስን አብሮ ለማጥናትና ለመጸለይ ምቹ ዕድል ፈጥረውላቸዋል። እነዚህ ስብሰባዎች በመኖራቸው ችግሮቻቸውን በግልጽ አንስተው ለመወያየትና አብረው ለመጸለይ አስችለ ዋቸዋል። በኢየሩሳሌም የሚገኙ ክርስቲያኖች በቤተ መቅደስ ለማምለክ ዕድል ከማግኘታቸው በስተቀር በሌላ ስፍራ የሚገኙ ክርስቲያኖች ለአያሌ ምዕተ ዓመታት የሚያመልኩበትና ኅብረት የሚያደርጉበት የራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ወይም የማምለኪያ ቦታ አልነበራቸውም። የጥንት ክርስቲያኖች ይህን የመሰለ ችግር ቢኖርባቸውም፥ በየክርስቲያኖች ቤት በመሰባሰብ አብረው ያመልኩና ይጽናኑ ነበር (የሐዋ. 12፥12፤ ሮሜ 16፥5 23፤ ቆላ. 4፥15፤ ፊል. 1–4)። የጥንት ክርስቲያኖች አብረው ይጽናኑና ይጸልዩ የነበረው በክርስቲያኖች ቤት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤት አደባባዮችና (የሐዋ. 19፥9) ፈቃድ ካገኙ ደግሞ በየሙክራቡ ይሰበሰቡ ነበር (የሐዋ. 14፥1–3፤ 17፥1፤ 18፥4)። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ የክርስቶስ ወንጌል በሁሉም ስፍራ ይሰበክ ነበር።

በአነስተኛ ቡድኖች ተሰብስቦ አብሮ መጽናናትና መጸለይ የተጀመረው በሐዋርያት ዘመን ሊሆን ይህ ልማድ ሊዘልቅ የቻለው ለጥቂት ዓመታት ብቻ ነበር። በመንግሥት በኩል የነበረው ስደት እጅግ ባየለባቸው ዓመታት አነስተኛ ቡድኖች እንደ መጠለያ ያገለግሉ ነበር። በዚህ ወቅት አዳዲስ አማኞች መሠረታዊ የክርስትናን እምነት አስተምህሮዎች ይማሩ የነበረው በእንዲህ ያለ መልክ ነበር። አያሌ አዳዲስ ክርስቲያኖች ወደ ክርስትና እምነት የመጡት ከአረማውያን ሃይማኖታዊ ልማድና አምልኮ ውስጥ በመሆኑ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመኖር ስለ ክርስትና እምነት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። በእነዚህ ቡድኖች አማካይነት በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ክርስቲያናዊ ሕይወትን አስመልክቶ የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት አግኝተዋል፤ በመሆኑም እንደ ክርስቲያን ከእነርሱ የሚጠበቀው ኀላፊነት ምን እንደሆነና በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው እንዴት እንደሚያድጉ መሠረታዊ ትምህርቶችን ተቀብለዋል።

በክርስትና ታሪክ ውስጥ አነስተኛ ቡድኖች ክርስቲያኖች በኅብረት እንዲቀመጡ፥ እርስ በርስ እንዲማማሩና በክርስቶስ ያገኙትን የጋራ ሕይወት እርስ በርስ እንዲካፈሉ ትልቅ እገዛ አድርገዋል። አነስተኛ የውይይት ቡድኖች

በቤተክርስቲያን ውስጥ ተሃድሶ እንዲመጣ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ለምሳሌ ጆን ዌስለ በ18ኛው ምዕተ ዓመት ላይ እንግሊዝን ከዳር እስከ ዳር ያጥለቀለቀ መንፈሳዊ መነቃቃት ሊያመጣ የቻለው በአነስተኛ ቡድኖች አማካይነት ነው። በ19ነኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ አነስተኛ የውይይት ቡድኖች በክርስቲያን ቤቶች ውስጥ ይደረጉ ነበር። በአንዳንድ ቦታዎች ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ግቢ፥ በመዝናኛ ቦታ ወይም በየሚያመቻቸው ስፍራ በመሰባሰብ በመንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸው ላይ ይወያዩ ነበር፤ በተለይ ደግሞ ራሳቸውን ለመንፈስ ቅዱስ እንዴት ማስገዛት እንደሚችሉ ይመካከሩ ነበር። እነዚህ ስብሰባዎች የቅድስናና የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴዎች እንዲያብቡ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። የቅድስናና የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴዎች፥ ክርስቲያኖች በተቀደሰ ሕይወት መመላለስ እንዳለባቸውና የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መታየት እንዳለበት ትልቅ ትኩረት የሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

በብዙ የዓለም ክፍሎች ክርስቲያኖች የሚካፈሉባቸው አነስተኛ ቡድኖች በየቤቱ ይደረጋሉ። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ቡድኖች ኢመደበኛ (ወይም መደበኛ ቅርጽ የሌላቸው) ሲሆኑ ሌላ ጊዜ ደግሞ መደበኛ (ወይም በሚገባ የተዋቀሩ) ናቸው። ከተለያየ የህይወት ዘይቤ፥ ማኅበራዊ ደረጃ፥ ሃይማኖታዊ ልማድና ሥርዐት የመጡ ክርስቲያኖች በአንድነት ተሰብስበው ኅብረት ያደርጋሉ፤ ያመልካሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናሉ፤ ይጸልያሉ። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ቡድኖች የሚደረጉት በቢሮዎችና በፋብሪካዎች ውስጥ ነው፤ የቢሮና የፋብሪካ ሠራተኞች ስብሰባቸውን የሚያደርጉት በምሳ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጪ ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ በስብሰባ ማእከሎችና በሆቴል አዳራሾች ይሰበሰባሉ። ብዙ ጊዜ የሚሰበሰቡት ግን በትምህርት ቤቶችና በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነው። እነዚህ ቡድኖች መደበኛ መልክ ኖራቸውም አልኖራቸውም፥ የሚሰበሰቡትም፥ በየትምህርት ቤቱ፥ በየቢሮውና በየመኖሪያ ቤቱ ቢሆንም ትልቁ ነገር እነዚህ ቡድኖች የሚሰበሰቡት የኢየሱስን ሕይወት እርስ በርስ ለመካፈልና ለመተናነጽ መሆኑ ነው።

በዓለም ላይ በሺህና በዐሥር ሺህ የሚቆጠር ምዕመናን ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት መደበኛ መልክ ያላቸውን ቡድኖች በማቋቋም ምዕመናኖቻቸው በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ። የእነዚህ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ ለምዕመናኖቻቸው የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ምግብና ምክር የሚሰጡት በእነዚህ ቡድኖች አማካይነት ነው።

በክርስትና ታሪክ ውስጥ የእነዚህ ቡድኖች ዓላማ የክርስቶስን ሕይወት በአንድነት መካፈል ነው። ክርስቲያኖች በእንዲህ ያለ መልክ ሲሰበሰቡ በመካከላቸው ጥልቅ መንፈሳዊ ኅብረት ይፈጠራል፥ የእያንዳንዱም ክርስቲያን መንፈሳዊ ጥያቄ ይመለሳል። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ አማኝ ከጌታ የተቀበለውን መንፈሳዊ ስጦታ የሚለማመድበት ስፍራ ያገኛል። በዚህ ዐይነት የክርስቶስ አካል የሆኑትንና ገና አማኝ ያልሆኑትን ሰዎች የሚያገለግልበት ዕድል ያገኛል።





ከኢየሱስ ዘመን ጀምሮ የነበሩ ክርስቲያኖች በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጠቃሚ መሆኑን እንደተረዱ እንተም ትረዳለህ። ከክርስቲያኖች ጋር እንዲህ ያለ ኅብረት ስታደርግ መንፈሳዊ ሕይወትህ ሲያድግና ሌሎች ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ አንተም ድርሻ እንዳለህ ትገነዘባለህ።

(6). ከእውነተኛው ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የክርስቲያኖች በአነስተኛ ቡድን መሰባሰብ በቅርብ ጊዜያት የተጀመረ ነገር ነው።
ለ. ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ሲመርጥ አነስተኛ ቡድን መፍጠሩ ነው።
ሐ. የአነስተኛ ቡድኖች ኅብረት በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያ ኖች ዘንድ የተለመደ ነበር።
መ. የሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች በቋሚነት በቤት ውስጥ እንደሚሰባሰቡ ያሳያል።
ሠ. የመጀመሪያዎቹ ምዕተ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በሺህ የሚቆጠሩ አዳዲስ አማኞች የክርስትናን መንገድ የተማሩት በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ነበር።
ረ. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመንፈሳዊ ተሃድሶ መስፋፋት አነስተኛ ቡድኖች አስተዋጽኦ አልነበራቸውም።
ሰ. በአሁኑ ወቅት የክርስቲያኖች በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ መካፈል በዓለም ዙሪያ የተለመደ ነገር ሆኖአል።
ሸ. አጅግ በርካታ አባላት ያላቸው ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት የትናንሽ ቡድን ህብረቶችን ማኪያሄድ አይመቻቸውም።
ቀ. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በየዘመናቱ የአነስተኛ ቡድን ህብረቶች ዓላማ የክርስቶስን ሕይወት በአንድነት መካፈል ነው።
በ. በአነስተኛ ቡድን ህብረቶች መካፈል ለመንፈሳዊ ሕይወት ያለው ጥቅም ትንሽ ነው።

## ግለሰቦች የሚያስፈልጋቸውን በአነስተኛ ቡድኖች አማካይነት ማሟላት

*ዓላማ 3 እያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ነገር አነስተኛ ቡድኖች ከሚሰጡት ጥቅም ጋር ማዛመድ።*

የሥነ ልቦና ሊቃውንት እንዳረጋገጡት ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶች አሏቸው። የሰው ልጆች አእምሮአዊ፥ ማኅበራዊ፥ አካላዊ፥ ሥነ ልቦናዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች አሏቸው። ክርስቲያኖች በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ሲሳተፉ እነዚህ ፍላጎቶቻቸው ይሟላሉ፤ በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ ፍላጎታቸው የበለጠ ይሟላል። እነዚህ ሁሉት ነገሮች አብረው የሚሄዱ ናቸው፤ ምክንያቱም የክርስቶስ ሕይወት የጋራ ሕይወት ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ ከክርስቶስ

ሕይወት ተካፍሰዋል። አሁን ትኩረታችንን ሰዎች ሁሉ በሚጋሩአቸው ወይም በሚካፈሉአቸው አራት ዋና ዋና ፍላጎቶች ላይ እንመልስ።

❶. *እያንዳንዱ ሰው ተቀባይነት ማግኘትን ይፈልጋል።* ማንነታችንን የምናውቀው በሰዎች መካከል ስንኖር ነው። በክርስቶስ ምክንያት ከሚወዱንና ከሚቀበሉን ሰዎች ጋር ስንኖር ማንነታችንን የበለጠ እያወቅን እንሄዳለን። በቤተክርስቲያን ውስጥ ካለን ኅብረት የተነሣ እንዲህ ያለ ግንኙነት መመሥረት ቢቻልም፥ ግንኙነቱ ጥብቅ መሠረት ሊኖረው የሚችለው ግን በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም የበለጠ መተዋወቅና መቀራረብ የሚቻለው ቁጥሩ አነስ ካለ ሰው ነው። ለምሳሌ አንድ ሕፃን ማንነቱን እያወቀ የሚያድገው በቤተሰቡ መካከል ነው። ልክ እንዲሁ አዲስ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ልጆችና የክርስቶስ አካል ሆነው ማንነታቸውን እያወቁ የሚያድጉት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ሲያደርጉ ነው። እያንዳንዱ ሰው መወደድ፥ ተቀባይነት ማግኘትና ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይፈልጋል። በክርስቲያናዊ ኅብረቶች ውስጥ የሚሳተፉ ክርስቲያኖች በዚህ ረገድ የሚያስፈልጋቸው ነገር ሲሟላ ያገኙታል።

❷. *እያንዳንዱ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግ ይፈልጋል።* ሰዎች ማኅበራዊ ፍጡር ናቸው፤ ሰው ማኅበራዊ ፍጡር ነው ሲባል እርስ በርሱ ኅብረትና አንድነት ያደርጋል ማለት ነው። በመላው ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ማኅበራዊ አንድነት ለማድረግ ከሚያስችላቸው ቡድን ጋር ይቀላቀሉ አለያም የራሳቸው ማኅበራዊ አንድነት ይፈጥራሉ። ከማኅበራዊ ኑሮ ተገልለው የሚኖሩ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው። ከሌሎች ሰዎች ጋር ኅብረትና አንድነት ለማድረግ እንድንችል ማኅበራዊ ሕይወቶችንና ከተሞችን እንገነባለን። እንደሚባለው ከሆነ የአንድ ኅብረተሰብ ማኅበራዊ ኑሮ እጅግ ውስብስብ እየሆነ በሄደ ቁጥር፥ አንዱ በሌላው ላይ የበለጠ ጥገኛ እየሆነ ይሄዳል። አንዳችን ለሌላው እናስፈልጋለን፤ ደግሞም አንዳችን ከሌላው ጋር ጥብቅ ግንኙነት ማድረግ እንፈልጋለን። በብዙ አቅጣጫ እያደግን የምንሄደው ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ነው። እኛ ለሌላው መስጠትና ከሌላው ደግሞ መቀበል ጤናማ የሆነ ማኅበራዊ እድገት ይፈጠራል። ልክ እንዲሁ በክርስቶስ አካል ውስጥ አንዱ ለሌላው ሲሰጥና ሌላው ደግሞ ከአንዱ ሲቀበል መንፈሳዊ እድገት ይገኛል። ለሌሎች የምንሰጠውና ከሌሎች የምንቀበለው እርዳታ ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ወሳኝ ነው። ከሌሎች ሰዎች ጋር የምናደርገው ኅብረት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ከሆነ ደግሞ ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል። ይህም በኅብረቱ መካከል እውነተኛ ፍቅርና መተሳሰብ እንዲኖር ያደርጋል። በዚህ ዐይነት ሁሉ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት ራሱን ይሰጣል።

❸. *እያንዳንዱ ሰው የየግሉን ነገር ለሌላው ለማካፈል ይፈልጋል።* ራሳችንን የምንመለከተው የየራሳችን የሆነ ማንነት ያለን ሰዎች አድርገን በመሆኑ የምናውቀውን፥ የምናስበውንና የምንፈልገውን ነገር ለሌሎች ለማካፈል እንሻለን። አንዳችን ለሌላው ስለምናስፈልግ የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግ እንፈልጋለን። ከሌሎች መማር እንፈልጋለን፤ እኛም የምናውቀውን ነገር





ለሌሎች ለማስተማር እንሻለን። ይህ ለሌሎች የማካፈል ፍላጎት በእያንዳንዳችን ውስጥ ሊፈጠር የቻለው እርስ በርስ ኅብረት ለማድረግ ካለን ምኞት የተነሣ ነው። ኢየሱስ በሕይወታችን ውስጥ ከሠራው ሥራ የተነሣ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚያስፈልገን ነገር ተሟልቶ ተሰጥቶናል፤ ይህም ለሌሎች በረከትና ጥቅም ሊሆን ተሰጥቶናል። የምናውቀውን ነገር ለሌሎች ስናካፍል፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እናድጋለን፤ ሌሎችም ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ምክንያት እንሆናለን።

❹. *እያንዳንዱ ሰው ያለውን ነገር ከሌሎች ጋር መካፈል ይፈልጋል።* ለሌሎች መስጠት እንዳለብን ይሰማናል፤ ደግሞም ማኅበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ አስፈላጊ እንደሆነ ይገባናል። ማንም ሰው ሁልጊዜ ከሌላ ሰው ተቀባይ ብቻ መሆን አይፈልግም። ሰዎች መሳተፍና የአቅማቸውን መርዳት ይፈልጋሉ። በሚደረገውና በሚሠራው ነገር ውስጥ ተሳታፊ መሆን እንፈልጋለን፤ ከሌሎች መቀበልና ለሌሎች መስጠት እንሻለን፤ ደግሞም ያለንን ነገር በልግስና መቸር እንወዳለን። በወንጌል ስብከት አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ፥ ስለ ኢየሱስ መመስከር፥ ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን መስለው እንዲያድጉ መርዳት፥ ወዘተ. . . እምነታችን ሕያው መሆኑን የምንገልጥባቸው ዕድሎች ናቸው። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ለናደርግ እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ክርስቲያናዊ ተግባሮች ውስጥ ለመሳተፍና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አብሮ ለማደግ ዕድል እናገኛለን።

እንግዲህ አነስተኛ የውይይት ቡድኖች እንደነዚህ ያሉ ፍላጎቶቻችን እንዲሟሉ ዐይነተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ክርስቲያን በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን እንደ ተሰጠው መጠን እያገለገለ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ዕድል ያገኛል። በእንዲህ ያሉ አነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚፈጠረው ትስስር፥ አንዱ ሌላውን ሌላውም አንዱን ከልቡ እንዲያገለግል መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። የእነዚህ ቡድኖች ዓላማ እንዲህ የመሰለው ነገር በአማኞች መካከል እንዲፈጠር ምክንያት መሆን ነው። የቡድኑ አባላት ጥሩ ነገር እንዲያገኙ ከተፈለገ የቡድኑ ሥራና ተግባር በሚገባ መነደፍ አለበት። በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ፍቅር፥ መተማመን፥ ለሌላው ማሰብ፥ ግልጽነትና ፈቃደኝነት ወሳኝ ነገሮች ናቸው። በመሠረቱ አንድ ሰው በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚያገኘው እንደዚህ ያሉ ባሕርያትን ነው።

(7). አራቱን የሰው ፍላጎቶች ከሚፈጸሙባቸው መንገዶች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| 1. ተቀባይነት የማግኘት ፍላጎት | 3. የማካፈል ፍላጎት |
| 2. የእርስ በርስ ግንኙነት ፍላጎት | 4. የመካፈል ፍላጎት |

ሀ. ፍቅርና ክብካቤ በሚታይበት መንገድ መስተጋብር ሲኖር ዕድገት ይኖራል።
ለ. ንቁ የሆነ መተሳሰብ በሚታይበት መንገድ ክርስቲያኖች በመስጠት እምነታቸውን ይገልጻሉ።
ሐ. አንድ ሰው አንድ የክርስቲያኖችን ኅብረት ሲቀላቀል ቤተሰባዊነት ይሰማዋል።

መ. እኛ ያለፍንበት ልምምድ ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚያ ልፉትን ይጠቅማል።

## የውይይት ቡድኖች ተግባራት

*ዓላማ 4 ከተሰጡት በርካታ አማራጮች ውስጥ የውይይት ቡድኖች ተግባራትን በትክክል የሚገልጸውን ዐረፍተ ነገር ለይ።*

የበሰለ ክርስቲያን ኀላፊነቱ ምን እንደሆነና እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ እንዴት መጠቀም እንደሚችል ያውቃል። እነዚህ ኀላፊነቶች በሦስት ክፍል ይመደባሉ። አንድ ክርስቲያን 1/ ለእግዚአብሔር 2/ ለራሱ እንዲሁም 3/ ለሌሎች ኀላፊነት አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ኀላፊነት አለበት፤ እርሱን ማምለክ፥ ማመስገንና ለእርሱ የሚገባውን ክብር ሁሉ መስጠት አለበት። ይህንንም በመጸለይና ከእርሱ ጋር ኅብረት በማድረግ እንዲሁም ለላደረገለት ነገር ሁሉ እርሱን በማመስገን ሊገልጽ ይችላል። ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ በንታመንና እርሱን ብቻ ተስፋ ለናደርግ እርሱን እንደምናመልክና እንደምናወድስ እንገልጻለን። በሁለተኛ ደረጃ አንድ የበሰለ ክርስቲያን ለራሱ ኀላፊነት አለበት፤ እንዲህም ሲባል ስለ ራሱ ጤናማ አመለካከት ሲኖረው ይገባል፥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግና እምነቱን በተግባር ማሳየት እንዳለበት ሊረዳ ይገባል ማለት ነው። ብርታቱንና ጥንካሬውን አስመልክቶ ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ ሲኖረው ይገባል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው አንድ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሙሉና ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚያድገው የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት እንደሚገባ ሲመግብና ሲከባከብ ነው። በሦስተኛ ደረጃ የበሰለ ክርስቲያን ለሌሎች ኀላፊነት አለበት፤ የክርስቶስ አካል ስሆኑና በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ላልተቀበሉ ሰዎች ኀላፊነት አለበት። አንድ ክርስቲያን እነዚህን ኀላፊነቶች ለመወጣት በቅድሚያ እርሱ ራሱ ከሌሎች ሰዎች መንፈሳዊ ምግብን ማግኘት አለበት፤ ከዚያም ከሌሎች ያገኘውን እርሱም በተራው ለሌሎች መስጠት አለበት። በዚህ ዐይነት ሁሉም የየራሱን ኀላፊነት መፈጸም ይችላል። የክርስቶስ አካል ክፍል በሆኑ መካከል የእርስ በርስ መተሳሰርና መተሳሰብ አለ።

በሚገባ የተደራጁ ወይም የተዋቀሩ አነስተኛ ቡድኖች እነዚህን ሦስት ኀላፊነቶች በትጋት እንድንፈጽም ያስችሉናል። የአነስተኛ ቡድኖች ተግባር ኅብረት ማድረግ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት፥ ማምለክ፥ መጸለይና ወንጌልን ማዳረስ ያካትታል።

ኅብረት የሚፈጠረው የእርስ በርስ መተሳሰብ ሲኖር ነው፤ የእርስ በርስ መቀባበል ሲኖር ነው። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች፥ ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስን ሕይወት እንደተካፈሉ የተረዱ ሰዎች ናቸው። የአነስተኛ ህብረት ቡድኖች አንዱና ትልቁ ተግባር ክርስቲያኖች ይህንን እውነት እንዲረዱና እንዲፈጽሙ መርዳት ነው። እነስተኛ ቡድኖች እርስ በርለ የሚተሳሰቡ ክርስቲያኖች ደስታቸውን፥





ሐዘናቸውን፥ ዕድገታቸውን፥ የልብ ስብራታቸውን፥ መንፈሳዊ ግንዛቤያቸውን፥ ጥያቄያቸውን፥ ችግራቸውን፥ ፍቅራቸውን፥ ጭንቀታቸ ውንና ሸክማቸውን የሚካፈሉበት ስፍራ ናቸው። ክርስቲያኖች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በግልጽ ሲነጋገሩ የሌላውን ሰው ሸክም እየተሸከሙና እየተካፈሉ ነው። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ለማድረግ እውነተኛ ፍቅር ያስፈልጋል፤ እውነተኛ ፍቅር ደግሞ የወንድማችንን ሸክም በደስታ እንድንሸከም ያስችለናል፤ ኅብረት ባለበት ቦታ መተሳሰብና መደጋገፍ አለ። መተሳሰብና መደጋገፍ ሲኖር ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወት አብሮ ማደግና ማበብ አለ።

በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን በመማር ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው። በዚህ ጊዜ ጥናቱ በገለጻ መልክ የሚደረግ ሳይሆን የቡድኑ አባላት በሙሉ ሊሳተፉበት በሚችል መልክ መሆን አለበት። የቡድኑ አባላት እርስ በርስ በመወያየት እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር አብረው ይፈልጋሉ፤ መጽሐፉ ስመጀመሪያዎቹ ተደራሲዎች ያለውን መልእክት አብረው ይመረምራሉ፤ በጥናታቸው ጊዜ ያገኙት እውነት ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አብረው ይመለከታሉ። የቡድን መጽሐፍ ቅዱለ ጥናት መሠረት የሌላቸው አውነቶች የሚነገሩበት ወይም ምንም የማያውቁ ሰዎች የሚወያዩበት ቡድን ተደርጎ መታየት የለበትም። ይልቁንም የቡድኑ አባላት ወደ ቡድኑ ከመምጣታቸው በፊት የሚያጠኑትን ክፍል በግላቸው በሚገባ አጥንተውና መርምረው ይመጣሉ፤ ከዚያም ለቡድኑ የሚጠቅም ሐሳብና ጥያቄ ይሰነዝራሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና፥ የምናጠናው ነገር ቀደም ሲል በትምህርት 7 ላይ በተመለከትነው መሠረት ከተዘጋጀ ስመንፈሳዊ ዕድገት ይረዳል። በጥናቱ ቡድን ውስጥ ያገኘናቸውን መንፈሳዊ እውነቶች ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ጋር ካዛመድን፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እናድጋለን፤ እያንዳንዱ አባል ከሚያጠናው መጽሐፍ እንዲሁም አብረውት ከሚያጠኑት ሰዎች ጋር ሲወያይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ይበስላል። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች የሚሰጡትን ሐሳብና የሚያቀርቡትን አስተያየት መቀበል ይማራል። በዚህ ዐይነት ሌሎች ሰዎች ስሚሰጡት አስተያየት መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባል። ከዚህ በላይ ግን የቡድኑ አባላት የእግዚአብሔርን ቃል እርስ በርስ እየተማሩ ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እርስ በርስ ይመካከራሉ።

እግዚአብሔርን ማምለክ ለእርሱ ክብርንና ምስጋናን መስጠት ያካትታል። ክርስቲያኖች ሲያመልኩ ስእግዚአብሔር ያላቸውን አክብሮትና ምስጋና ይገልጻሉ። ይህም በመዝሙር፥ በውዳሴ፥ በጸሎትና በምስክርነት ሊገለጽ ይችላል። ከእግዚአብሔር ታላቅነትና ማንነት ጋር የሚሄዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማንበብ፥ በጥንቃቄ የተመረጡ መዝሙሮችን መዘመርና የእግዚአብሔርን ባሕርይና ሥራ አስመልክቶ አስተያየቶችን መስጠት የእርሱን መገኘት እንድናስተውል ደግሞም መለኮታዊ ፍቅሩንና ኀይሉን እንድንረዳ ሊያደርጉን ይችላሉ። አነለተኛ ቡድኖች እንዲህ ያሉ መንፈሳዊ በረከቶችን እንድንካፈል የሚያደርጉ ዐይነተኛ ስፍራዎች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ላሉ መንፈሳዊ ተግባሮች ሰፊ ጊዜ የሚሰጠው መደበኛ በሆኑ የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ሳይሆን በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ነው። በአነለተኛ ቡድኖች ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ አምልኮ ትልቁን ቦታ መያዝ አለበት።

አነስተኛ ቡድኖች አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም «እርስ በርሳችሁ በመተጋገዝ ከእናንተ እያንዳንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም» (ገላ. ፀ፥2) የሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ የሚፈጸምበት ስፍራ ነው። ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውንና ሸክሞቻቸውን በጌታ ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው ለሆኑ ሰዎች ሲገልጹ እርስ በርስ በጸሎት መደጋገፍ ይፈጠራል። በዚህ ዐይነት አንዱ የሌላውን ሸክም በጸሎት ለእግዚአብሔር ያቀርባል። ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ኅብረት የምናደርገውና የልባችንን ሐሳብ ለእርሱ የምንገልጸው በጸሎት ነው። በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ልዩ ልዩ የጸሎት ዐይነቶችን ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ የቡድኑ አባላት በሙሉ አንድ ላይ ሊጸልዩ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ አንድ ሰው የቡድኑን አባላት ጥያቄና ልመና ይዞ ቡድኑን በጸሎት ሊመራ ይችላል። በጸጥታ መጸለይ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው የልቡን ሐሳብ ለእግዚአብሔር እንዲገልጽ ያስችለዋል። አንዱ የሌላውን ሸክም መሸከም የሚችለው አብሮ በመጸለይ ነው፤ ይህም እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው፤ የአነስተኛ ቡድኖች ተግባርም አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም እርስ በርስ መተጋገዝ ነው።

ወንጌልን መስበክ ደግሞ ያልዳኑ ሰዎች ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉትና የህይወታቸው ጌታ አድርገው እንዲከተሉት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አማካይነት መስበክ ነው። የአነስተኛ ቡድኖች አንዱ ተግባር ሰዎችን ከክርስቶስ ጋር ማስተዋወቅ ነው። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመምራት ልምድ ያለው ሰው የወንጌልን ዐቢይ መልእክት በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ለመናገር ዕድል ያገኛል። የቡድኑ አባላት ጓደኞቻቸውን ለመጋበዝ ነጻነት ይሰማቸዋል። አዳዲስ ሰዎች ወደ ታላላቅ ጉባኤዎች ከመሄድ ይልቅ እንዲህ ወዳሉ አነስተኛ ቡድኖች መሄድን ይመርጣሉ። የቡድኑ አባላት ያልዳኑ ጓደኞቻቸውን እንዲጋብዙ ማበረታታት ያስፈልጋል፤ ያልዳኑ ጓደኞቻቸው የወንጌልን እውነት ግልጽ በሆነ መንገድ የሚሰሙበት አጋጣሚ ሊሆን እንደሚችል ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

(8). ስለ አነስተኛ ህብረት ቡድኖች በተነጋገርነው መሠረት ከሚከተሉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትክክለኛ ተግባራት ከሆኑት በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ህብረትን አብሮ የመካፈል ጊዜ።
ለ. ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርጎ እንዴት መቀበል እንደሚቻል መናገር።
ሐ. በፖለቲካ ፖሊሲዎች ላይ መከራከር።
መ. የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከዕለታዊ ሕይወት ጋር እንዴት እንደ ሚዛመድ መወያየት።
ሠ. ለእግዚአብሔር ያለንን ፍርሃትና አክብሮት መግለጽ።
ረ. በመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ኃሳቦች ላይ ረጅም ገለጻዊ ትምህርት ማካሄድ።
ሰ. የምግብ አሠራርን የሚገልጹ መጽሐፍትን መሸጥ።
ሸ. የሌሎችን ችግር በመካፈል ክርስቲያናዊ ፍቅርን በተግባር መግለጽ።
ቀ. የእግዚአብሔርን ታላቅነት በመዝሙር መግለጽ።
በ. የወቅቱን ጉዳዮች አንስቶ መወያየት።





ተ. ለቡድን አባላት ችግር መጸለይ።
ቸ. ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ ሰዎችን መጋበዝ።

# አነስተኛ ቡድኖች ውጤታማ የሚሆኑበትን መርህ ማዘጋጀት

*ዓላማ 5 አነስተኛ ቡድኖች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርገውን መርህ በትክክል መለየት።*

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ለጋራ ዓላማ ሲሠሩ ትልቅ ነገር ያከናውናሉ። ለጋራ ዓላማ የሚሠሩ ሰዎች ትልቅ ነገር የሚያከናውኑት 1/ ቡድኑ ዓላማ ሲኖረው 2/ የቡድኑ አባላት ባሕርይ በቡድን ለመሥራት አመቺ ሲሆንና 3/ እያንዳንዱ አባል ግብ ሲኖረው ነው። የቡድኑን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚወስኑት እነዚህ ነገሮች ናቸው። የእርስ በርስ ግንኙነቶች፥ የመግባቢያ መንገዶችና የውሳኔ ደረጃዎች ሁሉ በቡድን ውይይቶች የተወሰኑ ናቸው።

ቡድኑን ውጤታማ ሊያደርጉት የሚችሉ አንዳንድ መርሆችን ከዚህ ውስጥ ማግኘት ይቻላል። የቡድኑ ተሳታፊዎችና የቡድኑ መሪዎች በቡድኑ ውስጥ ውጤታማ ሥራ መሥራት ከፈለጉ እነዚህን መርሆች ልብ ሊሉ ይገባል።

ልብ ልንለው ከሚገባው የመጀመሪያ መርህ ውስጥ አንዱ *«የቡድን ተሳትፎ»* የሚለውን ነው። የቡድኑ አባላት በሙሉ በቡድን መሥራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ሐሳባቸውን የመግለጽ ነጻነት ሊሰማቸውና ቡድኑ የደረሰበትን ድምዳሜና ውሳኔ የመቀበል ኀላፊነት ሊታይባቸው ይገባል። የቡድን ሥራውን እንዳለ ለመቆጣጠር የሚያስቡ ሰዎችን ይህ አዝማሚያ ትክክል እንዳልሆነ ማሳወቅ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ሌሎች የቡድኑ አባላት የበኩላቸውን ድርሻ የማበርከት መብት አላቸው። ደግሞም የሚፈሩና የበኩላቸውን ድርሻ ከማበርከት ወደ ኋላ የሚሉ ሰዎች የቡድኑ አባል እስከሆኑ ድረስ የእነርሱም ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ ያሻል።

አንድን ቡድን ውጤታማ ከሚያደርጉት መርሆች ውስጥ ሌላው መርህ ደግሞ *«የቡድን ተግባቦት»* ነው («ተግባቦት» የሚለው ቃል «ተግባባ» ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ሰዎች በሐሳብ ለመግባባት የሚያደርጉትን ንግግርና ውይይት የሚያመለክት ቃል ነው)። ይህም የሚባለው ነገር ምን እንደሆነ፥ እንዴት እንደሚባልና የሚያመጣው ለውጥ ምን እንደሆነ ያካትታል። ውጤታማ ተግባቦት ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ያካትታል፤ 1/ የሚነገረውን ቃል ወይም ሐሳባችንን ለመግለጽ የምንጠቀምበትን ቋንቋ 2/ የሚነገረውን ቃል የምንገልጽበት ድምፀት እና 3/ አካላዊ እንቅስቃሴ ናቸው። ውጤታማ ተግባቦት እንዲኖር ከተፈለገ እነዚህ ሦስት ነገሮች መኖር አለባቸው። የምንናገረው ቃል የሚያመለክተው አንድ ነገር ሆኖ ሳለ አካላዊ

አንቅስቃሴአችን ሌላ ነገር የሚያመለክት ከሆነ የተምታታ ነገር እያስተላለፍን ነው።

በተግባቦት ሂደት ውስጥ አንድ ሰው ለማስተላለፍ የሚፈልገው በኅሊናው ውስጥ ያለውን ሐሳብ ነው። ዓላማውም በኅሊናው ውስጥ ያለውን ሐሳብ ሌሎች አንዲረዱት ማድረግ ነው። በኅሊናችን ውስጥ ያለውን ሐሳብ ሌሎች እንዲረዱን ከተፈለገ ሐሳባችንን ግቡ በሆነ ቋንቋ መግለጽ አለብን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለመግለጽ የሞከርነውን ነገር በጥሞና የሚያደምጠን ሰው መኖር አለበት። በቡድን በምንሆንበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች ሐሳባችንን እንዲረዱን ከፈለግን በተቻለ አቅም በግልጽ መናገር አለብን፤ ግቡ በሆነ ቋንቋ ሐሳባችንን ካልገለጽን ሰዎች በትክክል ሊረዱን አይችሉም።

ውጤታማ ተግባቦት እንዲኖር የሚያደርገው ሌላው መርህ «የቡድን ድባብ» የሚባለው ነው። ይህም አንድ የቡድን አባል ለሌላው ሰው ያለውን አመለካከት ያመለክታል። በአንድ ቡድን ውስጥ ሙሉ ተቀባይነት የሚያገኙ ሰዎች አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ትችት ይገጥመናል ብለው የሚሰጉ ሰዎች አሉ። በአንድ ቡድን ውጤታማ ተግባቦት ሊኖር የሚችለው የቡድኑ አባላት ውስጣዊ ስሜታቸውን በግልጽ ለመናገር ሲደፍሩ ነው፤ የቡድኑ አባላት ማንም ሰው ትችትና ተቃውሞ ይደርስብኛል ብሎ እንዳይሰጋ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እያንዳንዱ አባል ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት መነጋገርና ሐሳቡን መግለጽ እንደሚችል ማወቅ አለበት፤ ከዚህ በተጨማሪ የሌሎች ሰዎችን ስሜት እንዴት መጠበቅ እንደሚችል ማወቅ አለበት።

(9). ከታች የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን ሁኔታዎች ቡድንን ውጤታማ ከሚያደርገው ትክክለኛ መርህ ጋር አዛምድ።

1. የቡድን ተሳትፎ 2. የቡድን ተግባቦት 3. የቡድን ድባብ

ሀ. አንድ ሰው ብቻ ሲናገር ሌሎች ዝም ብለዋል።
ለ. መጋቢ ዮሐንስ በመገኘታቸው ያዕቆብ ፍርሃት ተሰምቶታል።
ሐ. ሴትየዋ በታወራ አይናዋ ይናገራል።
መ. በሪሁን ምንም እንኳን ያልተማረ ቢሆን የሚናገረውን ሐሳብ ሁሉም ይቀበላሉ።
ሠ. የቡድኑ መሪ አባላት ሁሉ ሐሳባቸውን ለመግለጥ ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል።
ረ. የቡድኑ መሪ እያንዳንዱ ኃሳቡን አጥርቶና አስተካክሎ እንዲገልጽ ያበረታታል።
ሰ. በሪሶ የተነገረውን ነገር ምንም አላዳመጠም።
ሸ. የቡድኑ መሪ ኃሳቦች በግልጽነት እንዲንሸራሸሩ ያደርጋል።
ቀ. ወ/ት ብሌን አይነ አፋር በመሆኗ ሐሳቧን መግለጥ አትችልም።





# እነስተኛ ቡድኖችን መምራት

*ዓላማ 6 የውይይት ቡድኖችን የሚያደራጁና የሚመሩ ሰዎች የሚገጥማቸውን ችግር መለየት።*

ምናልባት በትንሽ የቡድን አገልግሎት ውስጥ የቡድኑ አባል በመሆን ወይም በሌላ መንገድ ተሳትፈህ ይሆናል። ምናልባትም በዚህ ትምህርት ውስጥ ካየሃቸው ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ክርስቲያን ቡድኖች ውስጥ ተሳትፈህ ይሆናል። እንዲሁም በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደተማርኸው አሉታዊና አዎንታዊ ነገሮችን በተሳተፍህባቸው ቡድኖች ውስጥ አስተውለህ ይሆናል። ምናልባትም በክርስቲያናዊ የውይይት ቡድኖች ውስጥ ቋሚ ተሳታፊ በመሆን የራስህን ድርሻ አበርክተህ ይሆናል። በክርስቲያናዊ የህብረት ቡድኖች ውስጥ ተሳትፈህ ከሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳደረገ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሕይወትህ እንድታድግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን እንዲመስሉ የበኩልህን ድርሻ እንድትወጣ የሚፈልግ መሆኑን እንደተረዳህ ተስፋ እናደርጋለን። ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ በምትረዳበት ጊዜ ቡድኑን እያደራጀህና እየመራህ ነው። የዚህ ትምህርት የመጨረሻው ክፍል አንድን ቡድን ስናደራጅና ስንመራ እንዴት ማደራጀትና መምራት እንዳለብን መሠረታዊ ግንዛቤ ይሰጠናል። የውይይት ቡድኖችን ስታደራጅና ስትመራ ከዚህ በታች የዘረዘርናቸው ነጥቦች መሠረታዊ ግንዛቤ ይሰጡሃል ብለን እናምናለን።

1. *ቡድኑ መሰብሰብ ያለበት የት ነው?* ክርስቲያናዊ የውይይት ቡድኖችን ስናደራጅ ቡድኑ የሚሰበሰበው የት ነው? የሚለው ጥያቄ ቀዳሚ ጥያቄ ነው። ለዚህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ሊሆን የሚችለው፥ ቡድኑ ዓላማውን ለመፈጸም እስከቻለ ድረስ የትም ሊሰበሰብ ይችላል የሚል ነው። በሆቴሎች፥ በቢሮዎች፥ በምሳ አዳራሾችና በፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰበሰቡ ቡድኖችን አይቻለሁ። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰበሰቡ ቡድኖችም አሉ፤ ይሁን እንጂ በርካታ ቡድኖች የሚሰበሰቡት በቡድኑ አባላት ቤት ውስጥ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ በቡድኑ አባላት ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ ቡድኖች ከሌሎቹ ይልቅ ተመራጭነት አላቸው። በቡድኑ አባላት ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ ቡድኖች በቢሮ፥ በሆቴል ወይም በፋብሪካና በምሳ አዳራሾች ውስጥ ከሚሰበሰቡ ቡድኖች ይልቅ የበለጠ ነጻነት አላቸው፤ የቡድኑ አባላት እንደልብ ለመወያየትና ለመነጋገር የሚያመቻቸው በቡድኑ አባላት ቤት ውስጥ ቢሰበሰቡ ነው። አንዳንድ ቡድኖች ሁልጊዜ የሚሰበሰቡት ከቡድኑ አባላት ውስጥ በአንደኛው ቤት ነው፤ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ በየተራ በቡድኑ አባላት ቤት ውስጥ ይሰበሰባሉ።

2. *ቡድኑ መሰብሰብ ያለበት መቼ ነው? በስንት ጊዜ ነው? ለምን ያህል ጊዜ ነው?* ሌላው ጥያቄ ቡድኑ መሰብሰብ ያለበት መቼ ነው? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችለው ለቡድኑ አባላት በሚያመቻቸው ጊዜ የሚለው ነው። ከቁርስ በፊት፥ በምሳ ሰዓት ወይም ማታ የሚሰበሰቡ ቡድኖችን አይቻለሁ። የቡድኑ አባላት በሙሉ በሚያመቻቸው ጊዜ የሚሰበሰቡ ከሆነ ይህ ትክክለኛ የመሰብሰቢያ ጊዜ ነው። የቡድኑ አባላት

መሰብሰብ ያለባቸው በስንት ጊዜ ነው? የሚለውም የሚወሰነው በቡድኑ አባላት ጊዜ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ያሉ ቡድኖች የሚሰበሰቡት በሳምንት አንድ ጊዜ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ያህል ነው። ሆኖም በየስንት ቀን ለምን ያህል ሰዓት መሰብሰብ እንዳለባቸው የሚወሰነው በቡድኑ አባላት ፍላጎትና ምርጫ መሆን አለበት። የውይይት ቡድኖች በሚደራጁበት ጊዜ ሁሉን ነገር እንደ ቡድኑ አባላት ጊዜና ሰዓት ለማቀናጀት መሞከር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፤ ገና ቡድኖቹ በሚደራጁበት ጊዜ ይህን ነገር ማሰብ ተገቢ ነው።

3. *በቡድኑ ውስጥ መሳተፍ ያለባቸው እነማን ናቸው?* በቡድኑ ውስጥ እነማን ይሰተፉ? የሚለው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። አንዳንድ ቡድኖች እንደ ወንጌል ስብከት ጣቢያ ለሚታዩ፥ የቡድኑ አባላት በአብዛኛው አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። ወንጌል በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ መሥራት ሲጀምር፥ ብዙዎች በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ይቀበላሉ፤ በዚህ ጊዜ የቡድኑ ይዘት መቀየር ይጀምራል። አንዳንድ ቡድኖች ለሴቶች ብቻ ይደራጃሉ፤ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ለወንዶች ወይም ለወንዶችና ለሴቶች ይደራጃሉ። አንዳንድ ቡድኖች ደግሞ በዕድሜ ደረጃ ይደራጃሉ፤ ለምሳሌ፦ ሀ/ ለወጣቶች፤ ለ/ ለወጣት ጎልማሶች፤ ሐ/ ለመካከለኛ ጎልማሶች እና መ/ ለጎልማሶች ቡድኖችን ማደራጀት ይቻላል። በርካታ ቡድኖች የሚመሠረቱት በጋራ ፍላጎት ላይ ነው፤ ስለዚህ በአንድ ቢሮ ወይም ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ፥ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ወይም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ቡድን ሊመሠርቱ ይችላሉ። ክርስቲያናዊ የውይይት ቡድኖች «የትም» ሊደራጁ ይችላሉ፤ ደግሞም በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግና ክርስቲያናዊ ኅብረት ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች ቡድን ሊመሠርቱ ይችላሉ።

4. *የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የቡድኑ አባላት ብዛት ምን ያህል መሆን አለበት?* ከመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ግብ ጋር የሚዛመደው ሌላው ነገር የቡድኑ አባላት ብዛት ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚናገሩት፥ የአንድ ቡድን አባላት ቁጥር ብዙ ሲሆን ብዙ ሥራ መሥራት ይቻላል። ይህ አባባል በስፖርቱ ዓለም እውነትነት ሲኖረው ይችላል፤ ሆኖም በህብረት ቡድኖች ውስጥ ውጤት የሚያመጣ አባባል አይደለም። ይህ አባባል በህብረት ቡድኖች ውስጥ ውጤት ሲያመጣ እንደማይችል እስቲ እንመልከት፤ የቡድኑ አባላት ብዛት ብዙ በሆነ ቁጥር በቡድኑ አባላት መካከል የሚኖረው የእርስ በርስ ግንኙነት የዛኑ ያህል ብዙ ይሆናል። ይህም ማለት በእያንዳንዱ አባላት መካከል ለሚደረገው የእርስ በርስ ግንኙነት (መስተጋብር) የሚኖረው ጊዜ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ እውነተኛ የሆነ የወንድማማች ኅብረት ለማድረግ የሚኖረው ዕድል ዝቅተኛ ይሆናል። የውይይት ቡድኖች የራሳቸው የሆነ ልዩ መለያ ባሕርይ አላቸው፤ የውይይት ቡድኖች ይህን ልዩ መለያ ባሕርይ ሲያጡ ለቡድኑ አባላት የሚሰጡት ትርጉም አነስተኛ ይሆናል፤ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ቡድን ሳይሆን እንደ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ይታያል። ሰዎች ሐሳባቸውን መግለጽም ሆነ እንደ ልብ መወያየት የሚችሉት የተወሰነ ቁጥር ባለው የእርስ በርስ ግንኙነት ውስጥ ነው። የአባላቱ ቁጥር ብዙ በሆነበት ቡድን ውስጥ ትርጉም ያለው ግንኙነት





ማድረግ አይቻልም፤ የቡድኑ አባላት የሚሰበሰቡት ከልብ በሆነ ፍላጎት ሳይሆን ምናልባትም በግድ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የአንድ ቡድን ቁጥር ከመጠን በላይ ከሆነ ትርጉም የለሽና ግብ የለሽ ይሆናል። እስቲ ለጥቂት ጊዜ ይህን አስብ።



ከዚህ በላይ በተመለከተው ሥዕል ላይ እንደምታየው፥ ሦስት አባላት ባሉት ቡድን ውስጥ ለድሰት የእርስ በርስ ግንኙነቶች ይደረጋሉ፤ በአራት አባላት ቡድን ውስጥ አሥራ ሁለት የእርስ በርስ ግንኙነቶች ይደረጋሉ፤ አምስት አባላት ባሉት ቡድን ውስጥ ደግሞ ሃያ የእርስ በርስ ግንኙነቶች ይደረጋሉ። የቡድኑ አባላት ብዛት ብዙ በሆነ ቁጥር የቡድኑ አባላት የሚያደርጉት የእርስ በርስ ግንኙነት የዛኑ ያህል ብዙ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ልምድ ያላቸው የቡድን መሪዎች እንደሚሉት፥ የአንድ ቡድን አባላት ቁጥር ከስምንት እስከ አሥራ ሁለት ቢሆን መልካም ነው፤ የቡድኑ አባላት ቁጥር ቢበዛ ቢበዛ እስከ አሥራ አምስት ቢደርስ የቡድን መለያ ባሕሪውን እንደጠበቀ ሊቀጥል ይችላል። ስለዚህ የአንድ አነስተኛ ቡድን አባላት ቁጥር አሥራ አምስት ከደረሰ፤ ቡድኑን ሁለት ቦታ ከፍሎ ሁለት ቡድን ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህ ቡድኖች ደግሞ ሲያድጉ እነርሱንም እንዲሁ ከፍሎ በአዲስ መልክ ማደራጀት ያስፈልጋል። ቡድኖችን በመምራት ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች እንደሚናገሩት ብዙ አባላት ካላቸው ቡድኖች ይልቅ ትንሽ አባላት ያላቸው ቡድኖች በፍጥነት ያድጋሉ። እንግዲህ የታሰበውን ውጤት ለማምጣት ከተፈለገ፤ አንድ የጥናት ቡድን አለር ሰዎችን፤ ግን ደግሞ ከአሥራ አምስት ያልበለጡ ሰዎችን መያዝ አለበት።

5. *ቡድኑን መምራት ያለበት ማን ነው?* ክርስቲያናዊ የህብረት ቡድኖችን የሚያደራጁ ሰዎች የሚያሳስባቸው ሌላው ጥያቄ ቡድኖችን ማን ይምራቸው? የሚለው ነው። ቡድኖችን የሚመሩ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ወደ አገልግሎቱ ይመጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ የህብረት ቡድኖችን የሚመሩ ሰዎች የሚሾሙት መጋቢዎች ወይም እረኞች ናቸው። መጋቢዎች የሚሾሙት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው፤ በመንፈሳዊ ዕውቀታቸው፣ ብስለታቸውና ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባላቸው ቦታ የተመሰከረላቸውን ሰዎች ነው። የቡድኑ አባላት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ቢሄዱ

ከመካከላቸው ለዚህ አገልግሎት ብቁ የሆኑ ሰዎች ብቅ ይላሉ። እነዚህ ሰዎች፤ ሌሎች ሰዎችን የመሳብና የማነቃቃት ባሕርይ አላቸው። ሌሎች ሰዎች ወደ አገልግሎት የሚመጡት የህብረት ቡድኖችን በተመለከተ በሚያሳዩት ልዩ ዕውቀትና ችሎታ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የአስተማሪዎችን ቡድን እንዲመራ ሊመረጥ ይችላል፤ ይህ ሰው የተመረጠው ከሌሎቹ አስተማሪዎች ይልቅ ሥልጠናና ልምድ ስላላቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ መሪዎች የሚመረጡት በአባላት ስምምነት ነው፤ ማለትም በቡድኑ አባላት ዘንድ የታወቁ ሰዎች በድምጽ ብልጫ ይመረጣሉ። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ቁራጥ አቋም ያላቸው ሰዎች በራሳቸው አነሳሽነት መሪ ይሆናሉ። የአንድ ቡድን አባላት ቡድኑን የሚመራውን ሰው ለመምረጥ በሚደረገው ሂደት ላይ የማይሳተፉ ከሆነ፤ ቡድኑ መንፈሳዊ ችግር ሊገጥመው ይችላል። የህብረት ቡድኖች ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ጥብቅ ዝምድና ሊኖራቸው ይገባል የተባለው ለዚህ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ መሪ ሌሎችን መቀስቀስ የሚችል፤ የተለየ ዕውቀትና ችሎታ ያለው መሆን አለበት። ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሰዎች ካለው ፍቅር የተነሣ ሌሎች ሰዎች ሊከተሉት ይፈልጋሉ። እንዲሁም መንፈሳዊ ዕውቀቱና ግንዛቤው ከሌሎች ሰዎች የሚበልጥ ከሆነ፤ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ሊረዳቸው ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ በቡድኑ አባላት ዘንድ የታወቀ ከሆነ፥ ቡድኑን እንዲመራ ለመመረጥ ያለው ዕድል ከፍተኛ ነው። ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመምራት ቅንአት ብቻ ሳይሆን ችሎታም ያስፈልጋል። ሁለቱንም የሚያሟላ መሪ ትክክለኛ መሪ ነው።

በክርስቲያናዊ የጥናት ቡድኖች ውስጥ የመሪዎች ተግባር ቡድኑን መምራትና የቡድኑ አባላት በእግዚአብሔር ቃል ላይ እርስ በርስ እንዲወያዩ ማበረታታት ነው። መሪው ጥናቱን ሊመራ ወይም ወንጌልን ሊሰብክ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ግን መሪው ቁጭ ብሎ አድማጭ ሊሆን ወይም ሌሎች ሊያስተምሩና ቡድኑን ሊመሩ እርሱ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል። የቡድኑ መሪዎች ሚና በቡድኑ ውስጥ ንቁ ውይይት እንዲኖር ማድረግና ቡድኑን ወደታለመለት ግብ ማድረስ ነው። ክርስቲያናዊ የህብረት ቡድኖችን አስመልክቶ የመሪዎች ግብ እያንዳንዱ ተሳታፊ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያድግበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ክርስቲያናዊ የህብረት ቡድኖች የሚመሰረቱበት ዋናው ዓላማ ማኅበራዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው። ክርስቲያናዊ የህብረት ቡድኖች የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ ከተፈለገ ይህን እውነት ልብ ማለት ያሻል።

ቀደም ሲል ለማመልከት እንደተሞከረው፥ የመሪዎች ሌላው ዐቢይ ተግባር የህብረት ቡድኖች ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ጋር ያላቸውን ትስስር መልክ ማስያዝ ነው። እንደ ፍጥረታዊ አካል ሁሉ መንፈሳዊም አካል ጠንካራና ጤናማ ሊሆን የሚችለው የአካል ክፍሎቹ (ብልቶቹ) በአንድነት ሲሠሩ ነው፤ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የራሱን ሥራ ሲሠራ አካሉ ያድጋል። እያንዳንዱ ቡድን የመላውን የክርስቶስ አካል ሥራ ሲሠራ ወንጌል ይስፋፋል፤ የወንጌል ፍሬ ይለቀማል፤ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ይበስላሉ። በህብረት





ቡድኖች አማካይነት የቤተክርስቲያን አባላት የተቀበሉትን ስጦታ የመለማመድ፤ ሌሎችን የመርዳትና በመንፈሳዊ ሕይወት የመብሰል ዕድል ያገኛሉ። አማኞች ባሉበት ስፍራ የተሰጣቸውን ኀላፊነት ሲፈጽሙ ወይም በተሰጣቸው ስጦታ ሲያገለግሉ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ታድጋለች። ንቁ መሪ የቡድኑ ዓላማ እውን እንዲሆን የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። የክርስቶስ አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ራሱን በተጠያቂነት ስር የሚያኖረው ለክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ የሕዝቡ እረኛ/ መጋቢ እንዲሆኑ ላደረጋቸው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እረኞች ጭምር ነው። እንዲሁም ዘወትር የሚተጋው የቡድኑ አባላት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና እንዲበስሉ እንጂ ሰው ተከታዮች እንዲሆኑ አይደለም። የህብረት ቡድኖች ፍሬያማ መሆን የሚችሉት ክርስቶስን ማእከል እስካደረጉና እርሱን ብቻ እስካከበሩ ድረስ ነው። የክርስቶስን አካል ለማነጽ ግብ ያላደረገ ቡድን ፍሬያማ ሊሆንና የክርስቶስን ዓላማ ሊፈጽም አይችልም።

(10). እውነተኛ ዐረፍተ ነገር ከሆነው ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የህብረት ቡድኖች በአመዛኙ የሚሰበሰቡት በአባላት ቤት ውስጥ አይደለም።
ለ. የህብረት ቡድኖች ለአባላት ሁሉ አመቺ በሆነው ጊዜና መጠን መገናኘት አለባቸው።
ሐ. በቡድኑ ውስጥ እነማን መሳተፍ እንዳለባቸው የሚወስነው እንደ ቡድኑ ፍላጎት ነው።
መ. የአባላትን መጠን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባ መመሪያ "አባ ላት በበዙ ቁጥር እያማረ ይሄዳል" የሚል መሆን አለበት።
ሠ. የአባላትን መጠን ለመወሰን ዋናው ጉዳን ለእርስ በእርስ ግንኙነት አመቺነቱ ነው።
ረ. መሪ ሊገኝ የሚችለው የሴሎችን አስተሳሰብ ለመቆጣጠር ችሎታ ያለው ሰው ሲገኝ ነው።
ሰ. እይነተኛ ክርስቲያን መሪ የቡድኑን እንቅስቃሴ ይመራል። ተከፋዮች በእንቅስቃሴው ውስጥ እንዲሳተፉም ያመቻቻል።
ሸ. ንቁ መሪ የቡድኑ እንቅስቃሴ ከቤተ ክርስቲያኒቱ እንቅስቃሴ ጋር የተስማማ እንዲሆን ያደርጋል።

(11). በትምህርታችን መሠረት መሪዎች የቡድኖቻቸው እንቅስቃሴ ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር የተስማማ እንዲሆን ሲያደርጉ ከሚገባበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት

ሀ. ቡድኑ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕግ የማይጠብቅ ከሆነ ቤተ ክርስቲ ያኒቱ ዕውቅና አትሰጠውም።
ለ. መጋቢያን እነርሱ የማይመለከቱትና የማይቆጣጠሩት ቡድን የሐሰት ትምህርት ይስፋፋበታል ብለው ስለሚሰጉ ብዙ አይወዱትም።
ሐ. እያንዳንዱ ክፍል ኃላፊነቱን ሲወጣ የአካል ኃላፊነት ከግብ ይደርሳል።

**10**

# በቤተ ክርስቲያን ማደግ

## ትምህርት

ግርማና ጸሐይ፡ ቤታቸው ለልጃቸው ለአማኑኤል ዕድገት የተመቸ ቤት እንዲሆን ዘወትር ይጥራሉ። ልጃቸው ደስ የሚሰኝበትና ዘወትር የሚያስታውሰው አስተዳደግ እንዲሆንለትም ይፈልጋሉ። ምክንያቱም ልጃቸው አንድ ቀን አንድ ጎልማሳ ሊወስድ የሚገባውን ኀላፊነት እርሱም እንደሚወስድ ያውቃሉ። ደግሞም የሚሠራውን ሥራና የሚያገባትን ሴት የሚመርጥበት እንዲሁም ልጅ የሚያሳድግበትና በሚኖርበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረውን ሚና የሚያውቅበት ጊዜ ይመጣል። ግርማና ጸሐይ የልጃቸውን ዕድገት የሚያዩት በሚያደርገው ነገር በመሆኑ ደስ ተሰኙ።

ልክ እንዲሁ ሰማያዊው አባታችን የእርሱ ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና ለክርስቲያናዊ አገልግሎት እንዲዘጋጁ ከአማኞች ጋር ኅብረትና አንድነት እንዲያደርጉ ይፈልጋል። በክርስትና ሕይወት እያደግንና እየበሰልን ለመሄድ የሚያስችለንን ነገር ሁሉ የምናገኘው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፤ ለአገልግሎት መዘጋጀት የምንችለውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው።

በዚህ የመጨረሻ ትምህርት ስለ ቤተክርስቲያን የምገባ አገልግሎት ጠቅለል ባለ መልኩ ታጠናለህ። ይህን ትምህርት ስታጠና፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ትገነዘባለህ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ቤተክርስቲያን፡- የመንፈሳዊ ምግብ ስፍራ
- ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚረዱ ፕሮግራሞች
- ሰዎችን ለአገልግሎት በማሠልጠን ማዘጋጀት
- ለምገባ አገልግሎት የተጠሩ አገልጋዮች





### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ትምህርት አጥንተህ ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ትማራለህ።

- ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ክርስቶስን እንዲመስሉ ቤተክርስቲያን ማድረግ ያለባትን ነገር መግለጽ ትችላለህ።
- ሦስቱ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የምገባ አገልግሎት መርህ ምን እንደሆኑ መናገር ትችላለህ።
- መጽሐፍ ቅዱሳዊው የአገልግሎት አሳቤ ምን እንደሆነና ክርስ ቲያኖችን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ከሚኖረው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት መግለጽ ትችላለህ።
- በቤተክርስቲያን የምገባ አገልግሎት ውስጥ የመጋቢዎችና የአስተማሪዎች ሚና ምን እንደሆነ መናገር ትችላለህ።

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር

## ቤተ ክርስቲያን፡-
## የመንፈሳዊ ምግብ ስፍራ

*ዓላማ 1 መንፈሳዊ ሕይወት በአጥቢያ ቤተክርስቲያን አማካይነት እንዴት መመገብ እንደሚችል መግለጽ።*

በጥቅሉ ሲታይ ቤተክርስቲያን በኢየሱስ አዲስ ሕይወት የተቀበሉትን አማኞች ሁሉ ታጠቃልላለች። ዳግም በተወለድህ ጊዜ የኢየሱስን አዲስ ሕይወት ተቀብለሃል፤ ደግሞም ከእርሱና የእርሱን ሕይወት ከተቀበሉ ሁሉ ጋር በመንፈስ አንድ ሆነሃል። እንግዲህ የመንፈሳዊው አካል ማለትም የቤተክርስቲያን አንዱ ክፍል ሆነሃል ማለት ነው። አዲስ ኪዳን «ቤተክርስቲያን» የሚለውን ቃል በሚጠቀምበት መንገድ ከተመለከትነው ቤተክርስቲያን ማለት ክርስቶስን ለመከተል የተጠሩ ሰዎች ማለት ነው። ይህ የክርስቶስ ተከታዮችን በአንድነት የሚይዘው አካል ቤተክርስቲያን ተብሎ ይጠራል።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ገጽታ አላት። በአንድ በኩል አለማቀፋዊ ገጽታ ሲኖራት፥ በሌላ በኩል ደግሞ አጥቢያዊ ገጽታ አላት። ቤተክርስቲያን አለማቀፋዊ ገጽታ አላት የሚለው ሐሳብ ጥቅል አነጋገር ነው። አለማቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን የምትይዘው የክርስቶስን ሕይወት በአዲስ ልደት የተቀበሉትን ሁሉ ነው። አለማቀፋዊ የተባለችውም ቤተክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ አማኞችን ስለምትይዝ ነው። አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተወሰነ ስፍራ የሚገኙ ጉባዔዎችን ነው። አጥቢያ ቤተክርስቲያን የአለማቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን መገለጫ ናት። ያለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አለማቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን ልትታወቅ አትችልም። እንግዲህ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተቤዡ ሰዎች ኅብረት

ስትሆን፥ የአለማቀፋዊቷን ቤተክርስቲያን ግብና ተልዕኮ ለመፈጸም በክርስቶስ አንድ የሆኑ ሰዎች ያሉባት ናት።

የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ራሱን በዚህ ምድር የሚገልጠው በቤተክርስቲያን አማካይነት ነው። ቤተክርስቲያን አሁን የምትሠራው፣ ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ወቅት ይሠራ የነበረውን ሥራ ነው። እርሱ የጀመረውን ሥራ ቤተክርስቲያን እንድትቀጥል መክሯታል (ማቴ. 26፥19-20፤ ማር. 16፥15፤ ሉቃ. 24፥46-49)። አጥቢያ ቤተክርስቲያን የአለማቀፍዋ ቤተክርስቲያን አካል እንደመሆኗ መጠን ጌታ የሰጠውን ትእዛዝ የመፈጸም ኀላፊነት አለባት። እያንዳንዱ አማኝ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አካል በመሆኑ፥ የሥራ ድርሻ አለው። በአዲስ ልደት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆኑ ሰዎች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አካል ወይም አባል መሆን አለባቸው። አማኞች መንፈሳዊ ሕይወታቸው ክርስቶስን እየመሰለ ለማደግ የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምግብ የሚያገኙትና ሌሎች ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማሳደግ የሚችሉበትን ዕድል የሚያገኙት በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። እነዚህን ሁለት ሐሳቦች እንዲህ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፦ «አጥቢያ ቤተክርስቲያን ክርስቲያናዊ ምገባ የሚከናወንባት ስፍራ ናት»።

ስለ ቤተክርስቲያን ባሕርይ የተሰጠው ይህ አጭር ገለጻ ሁለት ዐበይት እውነቶችን ልብ እንድንል ያደርገናል፤ ይኸውም፦

1/ እያንዳንዱ ክርስቲያን የአለማቀፉ የክርስቶስ አካል አባል ሲሆን በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚገኘው ሕይወት፣ ምስክርነትና ኅብረት ጋር አንድነት መፍጠር አለበት፤
2/ የክርስቶስ ተልዕኮ የእኛም ተልዕኮ ነው። የክርስቶስ ዓላማ ሰዎችን መዋጀትና እርሱን እንዲመስሉ መለወጥ ነው። የእርሱ አካል ክፍል የሆኑ ሁሉ የእርሱን ተልዕኮ፣ የእነርሱ ተልዕኮ ማድረግ አለባቸው። በተሰጠን ተልዕኮ ፍሬያማ መሆን የምንችለው በቃሉ ዕውቀት ስናድግና በሰጠን ስጦታ ስንጠቀም ነው። ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉት ወንጌልን ሳልሰሙ ሰዎች ወንጌልን ሲያሰሙና የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከእነርሱ ለሚያንሱ ሰዎች ሲያካፍሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የተረዱትን መንፈሳዊ እውነት ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር ሲያዛምዱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ይሄዳሉ። ክርስቶስ በሰጠን ሥራ ፍሬያማ ለመሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን መብሰል አለብን።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያጠናናቸው ትምህርቶች በአብዛኛው የሚዛመዱት ከአለማቀፍዋ ቤተክርስቲያን ጋር ሲሆን፥ በዚህ በመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ የምታጠናው ትምህርት የሚያተኩረው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ላይ ነው። ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተግባራት ውስጥ አንዱ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና እንዲበስሉ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ የምናገኘው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ





ሕይወታቸው እንዲያድጉና ክርስቶስን እንዲመስሉ መርዳት የምንችልበትን ዕድል የምናገኘው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው።

በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በአንድነት ስሙም ሆነው ሲሠሩ፥ አካሉ ያድጋል፤ የማያምኑ ሰዎችም በአካሉ ሕይወት ይማረካሉ። ከዚህ በተጨማሪ የክርስቶስ አካል ብልት የሆኑ አማኞች ሌሎችን ለማገልገል የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ምግብና ሥልጠና ያገኛሉ።

በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰበከው የእግዚአብሔር ቃል ሁለት ዐበይት ተግባራት ያከናውናል፤ 1/ የማያምኑ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ምክንያት ይሆናቸዋል፤ 2/ አማኞች እግዚአብሔርን የሚያስደስትና የሚያከብር ሕይወት መኖር እንዲችሉ መንፈሳዊ ምግብ ይሆናቸዋል። የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጥ ቢሆንም፤ ዓላማው ግን አንድ ነው፤ ቃሉን ስናስተምር፣ ስንሰብክ፣ ስንመክር፣ ስናበረታታና ስናጽናና ሰዎች ይለወጣሉ፤ ይታነጻሉ። የአማኞችን መንፈሳዊ ሕይወት በምንመግብበት ወቅት ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ፤ 1/ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይበስላሉ፤ 2/ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይዘጋጃሉ። እነዚህ እንግዲህ በእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት የሚገኙ ውጤቶች ናቸው።

አንድ ልጅ በነገር ሁሉ እያደገና እየበሰለ እንዲሄድ ከተፈለገ፥ ትምህርትና ሥልጠና እጅግ አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። አንድ ሕፃን ወይም ልጅ ልብሱን እንዴት መልበስና ራሱን እንዴት መመገብ እንዳለበት መማር አለበት። እንዲሁም እንዴት ስሜቱን መቆጣጠር፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር መኖርና ማንበብ እንዳለበት መማር አለበት። ልጆች በእነዚህ ነገሮች ላይ ለውጥ እንዲያሳዩ ከተፈለገ፣ ወላጆችና አስተማሪዎች በአንድነት ሊረዱቸው ይገባል። ልክ እንዲሁ ቤተክርስቲያን፣ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና እንዲበስሉ የአገልግሎት ዕድል ትሰጣለች።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት፣ የመንፈሳዊ ዕድገት የመጨረሻው ግብ ክርስቶስን መምሰል ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን በሄድን ቁጥር እየበሰልን እንሄዳለን። አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደበሰለ የምንለየው መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ ያየን እንደሆነ ነው። ክርስቶስን ለመምሰል ያለን ፍላጎት እርሱ እንዳገለገለ እኛም እንድናገለግል ያደርገናል፤ እንዲሁም ሌሎችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማሳደግ እንድንነሣሣ ያደርገናል። አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደበሰለ የምንለይበት ሌላው መንገድ ያ ሰው ጤናማ መንፈሳዊ ዕይታና ባሕርይ ያለው እንደሆነ ነው።

አሁን በትምህርት 2 ላይ *«ስድስት የፍላጎት ደረጃዎች»* በሚል ርዕስ ያጠናኸውን ከልስ። ይህን ስታደርግ ከመንፈሳዊ ልጅነት (ሕፃንነት) ወደ መንፈሳዊ ብስለት የሚደረገውን ሂደት አጢን። ከዚህ በተጨማሪ መንፈሳዊ ዕድገትና ብስለት ለክርስቲያናዊ አገልግሎት የሚያዘጋጅ መሆኑን ልብ በል። ክርስቲያናዊ ሕይወት ማለት ሰሚዎች ብቻ ሳይሆኑ አድራጊዎችም መሆን ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት መሰለፍ

የምእመናኖቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ብቁና ትክክለኛ በሆነ መንገድ መመገብና ማሳደግ ይችላሉ። ባንጻሩም በዕድሜ፣ በዝንባሌ፣ በሥራና በትምህርት ደረጃ መሠረት የተዋቀሩ አነስተኛ የህብረት ቡድኖች፣ ምእመናንን በሚገባ ለማሳደግና ለማገልገል ብርቱ መንገድ ናቸው። ሁለቱም መንገዶች እርስ በርስ የሚደጋገፉና የሚጠቀሙ ናቸው።

# ሰዎችን ለአገልግሎት በማሠልጠን ማዘጋጀት

*ዓላማ 3 ክርስቲያናዊ አገልግሎቶችን ለማሳደግ የምንጠቀምባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥልጠና መርሆችን መለየት።*

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምግባ አገልግሎት ውስጥ የመሪነት ሥልጠና ትልቁን ቦታ ይይዛል። እያንዳንዱ አማኝ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት ቀደም ሲል ተምረሃል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አከሌ አገልጋይ ነው፤ አከሌ ደግሞ አገልጋይ አይደለም፤ ወይም አከሌ ካህን ነው፤ አከሌ ደግሞ ካህን አይደለም የሚል ትምህርት ከቶ የለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንዲህ ያለው ልዩነት መከሰቱ በጣም የሚያሳዝን ነው። ክህነት ወይም ሹመት የተቀበሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ናቸው አገልጋዮች የሚለው አመለካከት በሰፊው ናኝቷል፤ ይሁንና ይህ አመለካከት ለአዲስ ኪዳን ባዕድ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት እያንዳንዱ አማኝ ክርስቲያናዊ አገልግሎትን ለመስጠት ተጠርቷል።

እርግጥ ነው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያሠለጥኑና እንዲያገለግሉ ኀላፊነት የሰጣቸውን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አኑሯል። ይህ በኤፌ. 4፥11-12 ላይ ያለ ግልጽ ትምህርት ነው። ቅዱሳን ማለትም የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥራ ሲያከናውኑ ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢያንና መምህራን ደግሞ ቅዱሳን ማገልገል እንዲችሉ ያዘጋጇቸዋል (ያሠለጥኗቸዋል፤ ያሳድጓቸዋል)።

ይህን ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰማ፣ ለዚህ ማን ይበቃል የሚል ፍርሃት ሳያድርብህ አይቀርም። በርካታ ክርስቲያኖች ይህን በመሰለው ፍርሃት ውስጥ ወድቀዋል። የፈራኸው ተገቢውን ሥልጠና ስላልወሰድህ ነው። ለአገልግሎቱ የማትበቃ አድርገህ ራስህን የገመትኸው እግዚአብሔር ለሰጠህ አገልግሎት እንዴት እንደምትዘጋጅ ስላልተነገረህ ነው። እግዚአብሔር መሪዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስቀመጠው አንተን እንዲያሠለጥኑህና እንዲያዘጋጁህ ነው። በበሰሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግር ሥር ሆነህ ስትማር፣ ክርስቶስን ለማገልገልና ሌሎችን ለማሳደግ ፍላጎት እያደረብህ ይመጣል።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ክርስቲያን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት የመጀመሪያውን እርምጃ ወስዷል። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እያንዳንዱ





የቤተ ክርስቲያን አባል ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲያገኝ አድርጓል። የመንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያንና በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ መገኘት ሁለቱንም ለአገልግሎት ብቁና ዝግጁ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ስጦታ (ስጦታዎችን) ሰጥቷል፤ ይህንንም ያደረገው አማኙ በክርስቶስ አካል ውስጥ ለአገልግሎት እንዲዘጋጅ ነው። እያንዳንዱ አማኝ ለአገልግሎት የሚሆነውን ስጦታ እንደተቀበለ አራት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ይመሰክራሉ። እነርሱም ሮሜ 12፥3-6፤ 1ቆሮ. 12፥1-11፤ ኤፌ. 4፥11-16፤ እና 1ጴጥ. 4፥10-11 ናቸው። እያንዳንዱ አማኝ ስጦታን ቢቀበልም፣ ሁሉም ግን አንድ ዐይነት ስጦታ አልተቀበሉም። ለአካሉ ብልቶች የተሰጠው ስጦታ ልዩ ልዩ ነው። አንዱ ስጦታ ሌላውን የሚሞላና የሚደግፍ ነው። በዚህ ዐይነት ሁሉም አካሉን ፍጹም ያደርጋሉ።

ቤተ ክርስቲያን አባላቷን በምታሠለጥንበትና በምታሳድግበት ወቅት ትልቁ ኀላፊነቷ ሁሉም ስጦታቸውን ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ ነው። አንድ አማኝ ስጦታውን ለይቶ ካላወቀ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ እንዴት ሊሠራ ይችላል? ጌታን ለማገልገል መመኘትና በአገልግሎት መማረክ፣ ስጦታችንን ለይቶ ለማወቅ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ጌታን ሲያገለግሉ ለናይ የእኛ ስጦታ ምን እንደሆነ መጠየቅ እንጀምራለን። አንድ ሰው በአንድ አገልግሎት ልቡ መማረክ ሲጀምር፣ በዚያ አገልግሎት ላይ እንዴት እንደሚሳተፍ መንገድ መፈለግ አለበት። እግዚአብሔር በእርግጥ ስጦታውን ሰጥቶት ከሆነ፣ ልቡ የተማረከበትን አገልግሎት ሲያገለግል እርካታንና ደስታን ያገኛል። አማኞች ያልተጠሩበት አገልግሎት እንዳለም ለይተው የሚያውቁት በዚህ ዐይነቱ ሂደት ነው። የተሰጠንንም ሆነ ያልተሰጠንን ስጦታ ለይተን የምናውቀው በዚሁ ጊዜ ብቻ ነው። አንድ ሰው የበሰሉ አማኞች በሚሰጡት ምስክርነት አማካይነት ስጦታውን ለይቶ ለማወቅ ይችላል፤ ምናልባት ይህ ዐይነተኛው መንገድ ነው። በስጦታው ሲያገለግል ሲያዩ፣ መንፈስም ሲሠራበት ሲመለከቱ፣ አገልግሎቱ በመንፈስ የተቀባ መሆኑን ወይም አለመሆኑን መለየት ይችላሉ። በውስጣቸው ያለው መንፈስ የስጦታውን እውነተኛነት ይመሰክርላቸዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዳበረታታውና እንዳነቃቃው (2ጢሞ. 1፥6) እነርሱም ይህን ሰው ማበረታታትና ማነቃቃት ይጀምራሉ። እንግዲህ ክርስቲያኖችን ለአገልግሎት የምናሠለጥንበትና የምናዘጋጅበት ትልቁ ዐላማ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታ ለይተው እንዲያውቁ ለማድረግ ነው።

የተሰጠንን ስጦታ ለይቶ ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም። የተቀበልነው ስጦታ ገና ያልተገራና ያልተሠራ ነው። ስጦታችንን በየጊዜው ማሳደግና ማጎልበት ይኖርብናል። ሌላው ቀርቶ እጅግ የሚያስደንቅ የሙዚቃ ክህሎት ያላቸው ሰዎች እንኳ ስጦታቸውን ለማሳደግ ዘወትር ልምምድና ብርቱ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራሉ። ቤተ ክርስቲያን በምግባ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ያለባት በዚህ ምክንያት ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመናንን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ያላቸውን ጊዜና ጉልበት ሁሉ መሠዋት አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን በመሪዎቿ አማካይነት ምዕመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታ እንዲያሳድጉ ስታደርግ ክርስቲያኖችን

ዋናው አስተማሪ እርሱ መሆን አለበት፤ ከእርሱ ጋር እንዲያገለግሉ ኀላፊነት የሰጣቸው ሰዎችም አብረውት ያስተምራሉ።

በኤፌ. 4፥11-12 መሠረት መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት የማዘጋጀት ኀላፊነት ተሰጥቷቸዋል። በተለይም የክርስቶስ አካል የሆኑ ሰዎች በዕውቀት፣ በእምነትና በመንፈሳዊ ዕድገት እየበሰሉ እንዲሄዱ የማድረግ ኀላፊነት አለባቸው። ማስተዳደርና ማገልገል የሚችሉ ሰዎችን ማሠልጠን፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው፤ ይህም ቢሆን የመጋቢዎች ኀላፊነት ነው። መጋቢ በሚያገለግሉ ሰዎች መካከል ቀዳሚ አገልጋይ መሆን አለበት። ዋና ተልዕኮውም መምራት የሚችሉ ሰዎችን ማፍራትና ማሠልጠን እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ነው። ይህ ተልዕኮ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ቦታ እንዲያውቁና የተቀበሉትንም መንፈሳዊ ስጦታ መለየት እንዲችሉ መርዳት ነው፤ ይህንንም ሌሎችን በማነጽ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያውሉት መደገፍ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ የመጋቢዎች ትልቁ ፈተና ሰዎችን ለዚህ ደረጃ ማድረስ ነው። ከእግዚአብሔር በታች ሆኖ ሰዎች ለዚህ ደረጃ እንዲበቁና ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲዘጋጁ ማድረግ እጅግ ታላቅ ኀላፊነትና ዕድል ነው። ኢየሱስ ይከተለው ከነበረው ብዙ ሕዝብ መካከል ጥቂት ሰዎች መረጠ። ከብዙ ሕዝብ መካከል ዐሥራ ሁለት ሰዎችን መርጦ አሠለጠነ። እንዲሁም ጳውሎስ ሊመሩና ሊያገለግሉ የሚችሉ ጥቂት ሰዎችን መርጦ አሠለጠነ። ጢሞቴዎስ አንዱ ሰው ነው። እንግዲህ የአንድ መጋቢ አስተማሪ ተልዕኮ ይህ ነው።

(11). የቤተ ክርስቲያን መጋቢ በጣም ጥቂት ጊዜ ቢኖረውና ሌሎች ተግባሮችን ትቶ እነዚህን ብቻ ሊያደርግ ይገባል የምትለውን ከየጥንዶቹ አንዱን ምረጥ።

ሀ. ወደ አዲስ አካባቢ በመሄድ ወንጌል ማሠራጨት።
ለ. የተወሰኑ ሰዎችን ሰብስቦ ስለ ወንጌል ሥርጭት ማስተማር።

ሐ. ከታመሙት ሁሉ የስልክ ጥሪ ራሱ መቀበል።
መ. የጉብኝት አገልግሎት የሚፈጽሙ ሰዎችን ማዘጋጀት።

ሠ. ወደፊት አስተማሪ የሚሆኑ ሰዎችን ማስተማር።
ረ. ጋዜጣ ላይ የሚወጣ ጽሑፍ ማዘጋጀት።

ሰ. ቤተ ክርስቲያኑን በአካባቢው ወዳለ አዲስ መንደር ማድረስ።
ሸ. ቤተ ክርስቲያኗን ወደ አዲስ መንደር የሚያደርሱ አገልጋዮች ማሠ ልጠን።

ቀ. በአንድ ለአንድ ወንጌል ሥርጭት ውስጥ መሣተፍ።
በ. በአንድ ለአንድ የወንጌል ሥርጭት ውስጥ የሚሳተፉ አምስት ሰዎችን ማሠልጠን።





ተ. አዳዲስ ሰዎች በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆሙ የክርስቲያናዊ ምግብ ፕሮግራም ማደራጀት።
ቸ. አዲስ የቤተ ክርስቲያን ህንጻ ዕቅድ ላይ በስፋት መሳተፍ።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋናው አስተማሪ መጋቢው ቢሆንም፣ የሚያስተምረው ግን እርሱ ብቻ ነው ማለት አይደለም። ምዕመናንን የመመገብና የመንከባከብ አገልግሎት ዘርፍ ብዙ በመሆኑ፣ አገልግሎቱ ብዙ አስተማሪዎችን ይፈልጋል፤ እግዚአብሔር ደግሞ ለዚህ አገልግሎት የሚሆኑ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። በመሆኑም አጥቢያ ጉባዔ ዎች እግዚአብሔር የማስተማር ስጦታ የሰጣቸውን አስተማሪዎች መለየት አለባቸው። ማስተማር ትልቅ ዐደራና ኀላፊነት ያለበት አገልግሎት ነው (ያዕ. 3፥1)። የማስተማር ስጦታ የተቀበሉ ሰዎች የአገልግሎቱን ታላቅነት ልብ ማለት አለባቸው፤ ምክንያቱም የብዙ ሰዎችን ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ የመለወጥ ትልቅ ዕድል አላቸው።

በቤተ ክርስቲያን የምገባ ፕሮግራም ውስጥ የሚያስተምሩ በርካታ ሰዎች፣ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩ ሰዎች ያላቸውን ዐይነት ሥልጠና የላቸውም። ምናልባትም እንዲህ ያለው ሥልጠና ለእነርሱ አስፈላጊ እንደሆነ አይታያቸውም፤ ያሁንና የያዙትን እውነት ለተማሪዎቻቸው በሚገባ ለማስተላለፍ ተገቢውን ሥልጠና መውሰድ ያስፈልጋቸዋል። በቤተክርስቲያን ውስጥ የማስተማር አገልግሎት ዓላማ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት በመሆኑ፣ ሌሎችን የሚያስተምሩ ሁሉ እነርሱ ራሳቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደጉና ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ ያወቁ መሆን አለባቸው። ዳግም ልደት ያገኙ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከጌታ ጋር ሕያው ሕብረት ያላቸውና በመንፈስ ቅዱስም የተሞሉ መሆን አለባቸው። ባሕሪያቸውም ኢየሱስ ያሳያቸውን ሕይወት መምሰል አለበት፤ ምክንያቱም የክርስቶስ ሕይወት ምሳሌ ናቸው።

የተሰጠ ሕይወት ያላቸው መምህራን ተለይተው የሚታወቁት በጸጋ እንዲያድጉ ለሚሰው የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት በሚሰጡት ምላሽና (2ጴጥ. 3፥18) የወንጌልን እውነት ለሌሎች ለማካፈል ባላቸው ቅንአት ነው (2ጢሞ. 2፥15)። እንዲህ ያሉ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃልና ስክርስቲያናዊ አገልግሎት ትልቅ ጥማት አላቸው። እንዲህ ቢባል በቤተክርስቲያን የሚያስተምሩ ሰዎች በዚህ ዙሪያ ያሉ ነገሮችን በሙሉ ማወቅ አለባቸው ማለት አይደለም። ማንም ሰው ሊታወቁ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ ላያውቅ ይችላል። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን የሚያ ስተምሩ ሰዎች መሠረታዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን ቃል የመተ ርተርና ከሕይወታቸውም ጋር የማዛመድ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ሰው ባሕርይና ስለ ተማሪዎቻቸው ሥነ ልቡና የተወሰነ ዕውቀት ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም ስለ ማስተማር-መማር ሂደት መሠረታዊ ዕውቀት ሊኖራቸውና ዕውቀታቸ ውንም እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲያሳስበው ክርስቲያን አገልጋዮች ሌሎችን የማስተማር ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል ብሎ ብሎታል (2ጢሞ 2፥2)።

ምናልባት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የማስተማር አገልግሎት ለመጀመር አስበህ ይሆናል። ምናልባትም እግዚአብሔር የማስተማር ስጦታ ስጥቶኛል የሚል ስሜት አድሮብህ ሊሆን ይችላል። ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ ዕድል ባገኘህ ጊዜ ሁሉ ስጦታህን ለማሳደግ መጣር አለብህ። ቀደም ባለው አንቀጽ ላይ ብዙ መሠረታዊ ነጥቦችን አንስተናል። እንግዲህ ራስህን ብዙ አገልጋይ ለማድረግ የምትችለው ያነሳናቸውን ነጥቦች ይበልጥ ለማወቅ ስትጥር ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ ለማቅረብ የሞከርሁት፣ ሌሎች ሰዎች ችሎታቸውን እንዲያሳድጉና በምግባ አገልግሎት ውስጥ ብቁ የሚያደርጋዋውን ዕውቀት እንዲገበዩ የረዳቸውን ነገሮች ነው። እነዚህ ነገሮች አሁንም ሆነ ወደፊት እግዚአብሔር የሰጠህን ስጦታና ችሎታ በምታሳድግበት ጊዜ ሁሉ እንደሚረዱህ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህንን ትምህርት ስትጨርስ፣ ይህን የተቀደሰ አገልግሎት ለማገልገል የሚረዳህን መሠረታዊ ዕውቀት አግኝተሃል። የተማርኸውን እንድትጠቀምበት እመክርሃለሁ። የተማርኸውን በሥራ ላይ ማዋል ስትጀምር በመንፈሳዊ ሕይወትህ ታድጋለህ፤ ሌሎች ክርስቶስን መምሰል እንዲችሉ መርዳት ትችላለህ።

(12). ከላይ በተሰጠው ትምህርት መሠረት ትክክለኛ የአገልግሎት ተግባ ሮችን ከትክክለኛ ሰዎቹ ጋር አዛምድ።

1. መጋቢዎች
2. አስተማሪዎች
3. መጋቢዎችና አስተማሪዎች
4. ክርስቲያኖች በአጠቃላይ

ሀ. የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥራና አገልግሎት ሁሉ በሚመለከት የመንፈሳዊ መሪነት ኃላፊነት።
ለ. የክርስቶስ አካል አባላትን ለአገልግሎት በማዘጋጀት የበሰለ አገልግሎት የማደራጀት ኃላፊነት።
ሐ. በእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ችሎታ ማዳበርና ሰዎችን ለአገልግሎት እንዲዘጋጁ ማድረግ።
መ. በክርስቶስ አካል አገልግሎት አማካኝነት ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ የማዳረስ ኃላፊነት።
ሠ. በክርስቶስ አካል አገልግሎቶች ውስጥ መሪ አገልጋይ።





## የሙከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት በል።

1. ሚዛናዊ የምግባ አገልግሎት እንዲኖር የወንጌል ሥርጭትን፣ ትምህርትን፣ ህብረትን፣ አምልኮንና ጸሎትን በሚመለከት ምዕመናን በሁሉም አቅጣጫ እንዲያድጉ ቤተ ክርስቲያን መርዳት አለባት።

2. ተከፋፍሎ በየመደቡ የሚሰጥ ፕሮግራም ማካሄድ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ተደርሶበታል።

3. ተከፋፍሎ በየመደቡ የሚሰጥ ፕሮግራም ተመሳሳይ የመማር ባህርያት ላሳቸው ተማሪዎች የሚቀርብ የትምህርት ፕሮግራም ነው።

4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ድርጅታዊ መዋቅር ቻርት የሚዘጋጀው በአገልግሎት ተመሳሳይነት ወይም በእድሜ ላይ ተመርኩዞ ነው።

5. አንድ ያሳደገ ክርስቲያን ሥጦታው ምን እንደሆነ መናገር ካልቻለ፣ ጌታን ለማገልገል ዝንባሌውን፣ መንፈሳዊ ሸክሙን፣ በግሉ የሚያስ ደስተውንና የሚያረካውን መመርመር ሥጦታውን ለማመልከት ይረዳዋል።

6. ክርስቲያኖች እየበሰሉ ሲሄዱ ሥጦታቸውን መለየት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ኃላፊነቶች እንዳልጠራቸውም መረዳት ይችላሉ።

7. በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ጥሩ ጥሩ አስተማሪዎች ካሉ መጋቢው አስተማሪም መሆን የለበትም።

8. የመጋቢው አንዱ ኃላፊነት ሌሎች የአገልግሎት ቦታቸውን እንዲለዩና የፀጋ ሥጦታቸውን እንዲያሳድጉና እንዲለማመዱ በመርዳት የመሪነትን አቅም ማጎልበት ነው።

9. በቤተ ክርስቲያን የምግባ ፕሮግራም ውስጥ የአስተማሪ መሠረታዊ ብቃት መለኪያ የመደበኛ ትምህርት ሥልጠና ነው።

## ክፍለ ትምህርት 7

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. እውነት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. እውነት
11. እውነት
12. ሐሰት
13. እውነት
14. እውነት
15. ሐሰት

## ክፍለ ትምህርት 8

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. ሐሰት

## ክፍለ ትምህርት 9

1. መ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሰ
5. ሐ
6. ሰ
7. ሀ
8. ሐ
9. ሀ
10. መ

## ክፍለ ትምህርት 10

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. ሐሰት